ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዉማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ፅሁፍ  አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር

ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማጎልበት ላይ ያለዉአስተዋጽኦ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሌ ኖኖ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

(የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ሙከራዊ ጥናት)

በ

አለምነሽ ካሳሁን

መስከረም 2014 ዓ.ም.

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማጎልበት ላይ ያለዉ አስተዋጽኦ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሌ ኖኖ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ሙከራዊ ጥናት)

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

በ

አለምነሽ ካሳሁን

አማካሪ፡ ኤባ ተሬሳ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ፡ ምህረት ሳዳሞ (ዶ/ር)

መስከረም 2014

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ-ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል ድህረ-ምረቃ

መረሀ-ግብር

ተማሪ ተኮር የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ማጎልበት ላይ ያለዉ አስተዋጽኦ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሌ ኖኖ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ሙከራዊ ጥናት)

በ

አለምነሽ ካሳሁን

| የፈተና ቦርድ አባላት ስም | ፊርማ | ቀን |
| --- | --- | --- |
| አማካሪ | | |
| -------------------------- | ----------------------- | -------------- |
| የዉስጥ ፈታኝ | | |
| ------------------------- | ------------------------ | ---------------- |
| የዉጭ ፈታኝ | | |
| -------------------------- | ------------------------- | ----------------- |

መስከረም 2014 ዓ.ም.

ጅማ፣ ኢትዮጵያ

# ማረጋገጫ

«ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ያለዉ አስተዋጽኦ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሌ ኖኖ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ሙከራዊ ጥናት)» በሚል ርዕስ በጅማ ዩኒቨርሲቲ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት ያልተሰራ የራሴ ስራ መሆኑንና የተጠቀምኳቸዉ ድርሳናት በትክክለኛ ዋቢዎች የተደረደሩና የጅማ ዩኒቨርሲቲም ጥናቱን ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለዉ መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**ስም-------------------------------------------**

**ፊረማ-------------------------** **ቀን----------------------**

# ምስጋና

ጥናቱን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ለረዳኝ እግዚአብሄር ምስጋና ይድረሰዉ፡፡ ከትልመ ጥናት እስከ መጨረሻ ድረስ አብረዉኝ ለቆዩ ለአማካሪዬ ለዶ/ር ኤባ ተሬሳ ምስጋናዬ ከልብ ነዉ፡፡ በመቀጠል የተሰጠኝን ርእስ በአግባቡ እንድፅፍ አሰተካክለዉ ለሰጡኝ ለደ/ር ምህረት ሳዳሞ ምስገናዬን አቀርባለሁ፡፡ እንዲሁም በትልመ ጥናት ላይ ስፊ ማብራሪያ በመስጠት ሃሳቤን ሰፋ አድርጌ የመግለፅ አቅም እንዲኖረኝ ላደረጉን ለዶ/ር ጥበቡ ሽቴ ምስጋናዬ ከልብ ነዉ፡፡ እንዲሁም ለ9ኛ ክፍል ተተኳሪ ተማሪዎች ማለትም በጥናቱ ተሳታፊ ሆነዉ ለቀረቡት ተማሪዎች እና ለብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህር እና በአንዳንድ ነገሮች ላይ ለረዱኝ የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡ እንዲሁም ለቤተሰቦቼ፡፡

## አጠቃሎ


*የዚህ ጥናት አላማ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሌ ኖኖ ብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ተኮር የማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉ አስተዋጽኦ መፈተሸ ነዉ፡፡ ከዚህ አጠቃላይ ከግብ ላይ ለመድረስ ሙከራዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ ሆኗል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ አንድ የአማርኛ መምህር እና የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ናቸዉ፡፡ ተማሪዎች እና ትምህርት ቤቱ በአመቺ ናሙና የተመረጡ ሲሆን መምህሯ  በጠቅላይ ናሙና በመመረጥ ተሳታፊ ሆነዋል፡፡ እንዲሁም ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጡት መሳሪያዎች ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸዉ፡፡ ከፈተና የተገኘዉን ዉጤትም በመጠናዊ ገላጭ ዘዴዎች ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ፈተናዉም ቅድመ-ትምህርት ፈተና እና ድህረ-ትምህርት ፈተና ሲሆኑ ለቁጥጥር ቡድን እንዲሁም ለሙከራ ቡድን  ፈተናዉን አዘጋጅቶ በመፈተን  ከፈተናዉ የተገኘ ዉጤት በባዕድ  ናሙና ቲ-ቴስት የተሰላ ሲሆን በቅድመ ልምምድ የሙከራ ቡድን አንብቦ መረዳት ዉጤት በአማካይ=28.85፣ መደበኛ ልይይት=2.9137፣ በድህረ-ልምምድ አማካይ=33.3፣ መደበኛ ልይይት =3.1881 የቲ-ቴስት ዋጋ ባለሁለት ጫፍ በመሆን ጉልህ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህ ክፍተትም የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በሳምንት አንዴ መሆኑ ተማሪዎች የንባብ ጊዜን በስፋት እንዳይጠቀሙት አድርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎች አንድን ነገር አንብበዉ እንዳይረዱ ያደርጋል፡፡ የተማሪዎችን የማንበብ ልምድ የሚያዳብሩ የትምህርት ዘዴዎችን ተጠቅመዉ የቋንቋ ትምህርቱን አለመስጠት ነዉ፡፡ ለጥናቱ ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ሊሆኑ ይችላሉ የተባሉት፡- የአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ እንደ ሌሎቹ ትምህርት በሳምንት ሶስት ቢሆን ምንባቦችን ከሰዓት አንጻር አንዴ ብቻ ከሚያነቡ አንዱን ክፍለ ጊዜ የንባብ ጊዜ በማለት በማያሰለች መልኩ እንዲያነቡ ያደርጋል፡፡*

# ማዉጫ


| ይዘት | ገፅ |
|---|---|
| ምስጋና | i |
| አጠቃሎ | ii |
| ማዉጫ | iii |
| የሰንጠረዥ ማውጫ | vi |
| ምዕራፍ አንድ | 1 |
| 1. መግቢያ | 1 |
| 1.1. የጥናቱ ዳራ | 1 |
| 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት | 3 |
| 1.3.የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች | 4 |
| 1.4. የጥናቱ አላማ | 4 |
| 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ | 4 |
| 1.6. የጥናቱ ወሰን | 5 |
| 1.7. የጥናቱ ዉስንነት | 6 |
| ምዕራፍ ሁለት | 7 |
| 2. ክለሳ ድርሳናት | 7 |
| 2.1. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት | 7 |
| 2.1.1. የተማሪ ተኮር አቀራረብ መርሆች | 10 |
| 2.1.2. የንባብ ብያኔ | 11 |
| 2.1.3. የንባብ አይነቶች | 14 |
| 2.1.3.1. የፍጥነት ንባብ | 14 |
| 2.1.3.2. የዝግታ ንባብ | 15 |
| 2.1.3.3. ሰፊንባብ | 15 |
| 2.1.3.4. ጥልቅ ንባብ | 15 |
| 2.1.4. የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት | 15 |
| 2.1.5. የንባብ ትምህርት አቀራረብ | 16 |
| 2.1.5.1. ቅድመ ንባብ | 16 |

2.1.5.2. የንባብ ጊዜ ...................................................................................... 17

2.1.5.3. ከንባብ በኂላ ...................................................................................... 17

2.1.6. የአንብቦ መረዳት ምንነት ...................................................................... 17

2.1.7. የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶች ............................................................ 20

2.1.8. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃዎች ........................................................... 21

2.1.9. የአንብቦ መረዳት ክሂል አስፈላጊነት ......................................................... 22

2.1.10. የመምህሩ ሚና ...................................................................................... 23

2.1.11. የተማሪዉ ሚና ...................................................................................... 24

2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ................................................................................. 25

ምዕራፍ ሦስት ................................................................................................ 28

3. የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ ................................................................................... 28

3.1. የጥናቱ ንድፍ ................................................................................................ 28

3.2 የጥናቱ አካላይ ............................................................................................ 28

3.2.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ................................................................................ 28

3.2.2. የትምህርት ቤት ምርጫ ............................................................................ 28

3.2.3. የመማሪያ ክፍል ምርጫ ............................................................................ 29

3.2.4 የተጠኚዎች ምርጫ ..................................................................................... 29

3.2.5. የመምህር አመራረጥ ................................................................................. 29

3.3. የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ ................................................................................. 29

3.3.1. አንብቦ መረዳት ፈተና .............................................................................. 30

3.3.2. የፅሁፍ መጠይቅ ...................................................................................... 31

3.4 የማስተማሪያ መሳርያ ዝግጅትና የማስተማር ትግበራ ............................................... 32

3.4.1 የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት ..................................................................... 32

3.4.2 የማስተማር ትግበራ ................................................................................... 32

3.5. የመረጃ መተንተኛ ዘዴ .................................................................................... 34

ምዕራፍ አራት…………………………………………………………………………………35

4.የመረጃ ትንተና እና ማብራርያ………………………………………………………...........35

4.1የመረጃ ትንተና------------------------------------------------------------------------------------35

4.1.1 ከፈተና የተገኘ መረጃ ትንተና…………………………………………………………….35

4.1.2 ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና........................................................................ 388

4.2 የዉጤት ማብራሪያ .................................................................................................... 44

ምእራፍ አምስት............................................................................................................... 46

5. ማጠቃለያና አስተያየት ................................................................................................ 46

5.1 ማጠቃለያ ................................................................................................................ 46

5.2 አስተያየት................................................................................................................. 47

ዋቢ ፅሁፎች .................................................................................................................... 48

አባሪ 1 ............................................................................................................................ 52

አባሪ 2 ............................................................................................................................ 54

አባሪ 3 ............................................................................................................................ 57

አባሪ 4 ............................................................................................................................ 61

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1. የሁለቱን ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት የሚያሳይ ........ 35
ሰንጠረዥ 2. የሁለቱ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ........ 36
ሰንጠረዥ 3. የድህረ-ፈተና ትምህርት ዉጤት ........ 36
ሰንጠረዥ 4. የድህረ ልምምድ ፈተና ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያሳይ ........ 37
ሰንጠረዥ 5. በመማር ማስተማር ጊዜ የመምህርን የክፍል ውስጥ ተግባር የሚያሳይ ........ 38
ሠንጠረዥ 6. ስለ ቅድመ ልምምድ  ያላቸዉን ግንዛቤ የሚያሳይ ........ 41
ሰንጠረዥ 7 በመማር ማስተማር ጊዜ የተማሪዎችን ተግባር የሚያሳይ፡፡ ........ 42

# ምዕራፍ አንድ
# መግቢያ

## 1.የጥናቱ ዳራ

ትምህርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ልማት የሚበጅ ዜጎችን ለማፍራት የሚያስችልና የህብረተሰቡን አመለካከት ወደ ሚፈለገዉ አቅጣጫ የሚለዉጥ ከአዲስ ቴክኖሎጂ ዉጤትና ሳይንሳዊ ግኝቶች ጋር በማስተዋወቅ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና ባህላዊ እድገቶችን የሚያፋጥን መሳርያ ነዉ፡፡

ተማሪ-ተኮር የመማር-ማስተማር ሂደት የተማሪዉን እዉቀት/ችሎታ/መሰረት በማድረግ የሚከናወን የማስተማር ዘዴዎችን በስፋት የያዘ ነዉ፡፡ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዉ ለመማር ያለዉን ፍላጎት እና አንድ የተወሰነ ርዕሰ ጉደዳይ መርሃ ግብሩን እንዴት እንደሚማሩ ለተማሪዎች ሀላፊነት በመስጠት የተማሪዉን በራስ የመተማመን ችሎታን ያዳብራል፡፡

እንዲሁም ተማር ተኮር ትምህርት ለተማሪዉ ተሞክሮ እንደ ማእከላዊ እዉቅና በመስጠት የተማሪዉን ፍላጎት ያስቀድማል፡፡ ይህ የማስተማር ስነ ዘዴ ዉጤታማ የመማር ማስተማር ስራ ከሚከናወንባቸዉ መንገዶች አንዱና ዋነኛዉ ተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴዉን ተግባራዊ ማድረግ ነዉ፡፡

መምህራን ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴን ተጠቅመዉ ሲያስተምሩ የተማሪዎችን የትምህርት ዉጤት ከማሳደጉም በላይ ተማሪዎች እራሳቸዉን በመማር ማስተማር ተግባር ላይ ዋና ተዋናይ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ለምሳሌ አንድ ርዕስ በመስጠት ስለ ርዕሱ አላማ፣ ጥቅም ያለምንም ፍራቻ እንዲገልፁ የሚያደርግ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ምኝጭ የኢትዮጵያ መምህራን መድረክ (Afar national regional state Education bureau 2015)፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳዉ ተማሪ-ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ በአንብቦ መረዳትላ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ከሂሎችንም የሚያዳብር መሆኑን እንረዳለን፡፡

እንደ Stern (1983) አገላለፅ ቋንቋ መማር ማለት የቋንቋ ክህሎችን ማወቅና ማጎልበትን ያጠቃልላል፡፡ ይህ ማለት የራሱ የሆነ የትምህርት መርሀ-ግብር ወጥቶለት፣ ትምህርት ቤት በመግባት መደበኛ በሆነ መንገድ የቋንቋውን ህግጋት እና ስርዓት ባለውና በሙሉ ንቃት ወይም በይሁንታ ማወቅ ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋ መማር በቋንቋው የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የመፃፍና የማንበብ ክሂሎችን መገንባት ማለት ነው፡፡

የአፍ መፍቻም ሆነ ሁለተኛ ቋንቋ መደበኛ በሆነ መንገድ የመማር-ማስተማሩ ሂደት የቋንቋውን ህግጋትና ውስጣዊ መዋቅር አሳውቆ በተግባቦት ለማብቃት ትልቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ለዚህም ሲባል በተለያዩ የቋንቋ ማስተማር ዘዴዎች በመጠቀም በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ሲሰጥ ቆይቶ አሁን ካለበት ተግባቦታዊ የማስተማር ዘዴ ላይ ተደርሷል፡፡ እንደሌሎች ዘዴዎች ሁሉ የተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የለውጥ ሂደትም ረጅም

እድሜን አስቆጥሯል፡፡ በRichards & Rodgers (1986) አገላለጽ የማስተማሪያ ዘዴዎቹም ብዙ ሲሆኑ የመለወጥ ሂደታቸውም በአንዱ ዘዴ ደካማ ጎን ላይ ማሻሻያዎች እየተደረገለት አሁን ዘመናዊ በተባለበት ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ ላይ ደርሷል ፡፡

Piaget (1911) ተማሪዎች አዳዲስ ልምዶችን እና ግኝቶችን በማስተባበር በእዉቀትና በማስታወሻ መንገድ እንደሚገነዘቡ ይገልፃል፡፡ ይህም ሀሳቡ ትምህርትን ከእዉነተኛ የሒዎት ሁኔታዎች በማገናኘት የተማሪዉን ዉስጣዊ ግፊት ለይ ያተኮረ ነዉ፡፡ ዉስጣዊ ግፊት ስንል የተማሪዉን ለድርግ ወይስ አላድርግ የሚለዉን ጥያቄ የሚያሳይ ነዉ፡፡ ስለዚህ ይህ ተማሪ - ያማከለ ትምህርት ተማሪዉ በራሱ በመተማመን የተሰጠዉን ርዕሰ ጉዳይ ያለፍራቻ ሲገልፅ በርዕሱ ዙርያ ያልተንዛዛ/ግራ የማያጋባ ግልፅ የሆነ ፍቺ ስለሚሰጠዉ ለተማሪዉ ጥሩ ዉጤት ያሰጠዋል፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን ተማሪዉ ትምህርቱን በሚማርበት ጊዜ የሚማረዉ ርእስ ካለዉ እዉቀት ጋር ስለሚመጣጠን የተሰጠዉን ርዕሰ ጉዳይ በደንብ ተዘጋጅቶበት ስለሚያቀርብ አይረሳዉም፤ ተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ በክፍል ዉስጥ ተማሪዎች በመምህራቸዉ ብቻ ጥገኛ አይሆኑም፡፡ Johnes (2007) እንደሚያብራራዉ ለትምህርት ገለፃ፤ ለሚሰሩት ተግባራት፤ ለእርማት ለምክክር መምህራንን ለመጠበቅ አይገደዱም፡፡

በመቀጠልም ተማሪን ያማከለ ትምህርት በምናስተምርበት /በምናከናዉንበት/ጊዜ በጣም አስፈላጊ ሀሳቦችን በትምህርቱ ዉስጥ በማስገባት በአካልና በአእምሮ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማድረግ ማስተማር አለብን፡፡ ይሄንን በምናደርግበት ጊዜ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊዎች ይሆናሉ ይላል፡፡

ተማሪ-ተኮር የማስተማር ስልቶች በተግባር ዉሰጥ የተማሪዉን ትርጉም ያለዉ ተሳትፎ የሚፈልግ ሂደት ነዉ፡፡ ማለትም በእዉነተኛዉ የሒይወት ሁኔታ ዉስጥ ትምህርቱን እንዲረዱት እንዲያብራሩት፤ እንዲተገብሩት እና ማስተላለፍ የሚያስችላቸዉን ማንኛዉንም የትምህርት ሂደት እንዲገልጹ የሚያደርግ ነዉ፡፡

ተማሪ ተኮር ትምህርት በምናከናዉንበት ጊዜ የተለያዩ ምክንያቶች ላይ በመመስረት የተለያዩ ክንዉኖችን ማከናወን አለብን፡፡ ክንዉኖቹም ቡድን ስራዎች ችግር አፈታትን ጥያቄን ያጠቃልላል ፡፡ ተማሪ ተኮር ትምህርት በምናስተምርበት ጊዜተማሪዎች የቡድን ስራም ሆነ የግል ስራ በሚሰሩበት ጊዜ በችግሩዙርያ የራሳቸዉን ሀሳብ በመግለጽ ለችግሩ ግንዛቤ

እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፡፡ ችግሩ ምን ሊሆን ይችላል በማለት የመፍትሄ ሀሳብ እንዲሰጡም ያደርጋል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ተማሪ-ተኮር ትምህርት የተማሪዉን እዉቀት/ችሎታ/መሰረት በማድረግ የሚከናወን የማስተማር ዘዴ ነዉ፡፡ ተማሪዉ ለመማር ያለዉን ፍላጎት የሚያነሳሳ እንዲሁም አንድ የተወሰነ ርዕሰ ጉዳይ፣መርሃ ግብሩን እንዴት መምራት እደሚችሉ በችሎታ ማስተማርን ለተማሪዎች ሀላፊነት በመስጠት የተማሪዉን በራስ የመተማመን ችሎታን የሚያዳብር ነዉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የማስተማሪያ ሞዴሎች በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ለይ ጉልህ ሚና እንዳላቸዉ ከዚህ በፊት ከተጠኑት ጥናቶች ለማረጋገጥ ተችሏል ለምሳሌ ያክል ፋሲካ ዉበቱና አገኘሁ ተስፋ (2009) በአገኘዉ(1990) የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከሌሎች ክህሎች በ11ኛ ክፍል መማርያ መጽሐፍ ዉስጥ ትኩረት የተሰጠበት በመሆኑ በትብብር መማር በተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት ለይ ያለዉ ሚና በሚል ርዕስ ጥናት አካሂደዉ ባካሄዱት ጥናት ላይም ይህ የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ጉልህ ሚና እንዳለዉ በጥናታቸዉ አረጋግጠዋል፡፡

እንዲሁም አንድነት ይርጉብ (2010) በባቶ ሙሉ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ትምህርተ ማስተማርያ ሞዴል በአንብቦ መረዳት ክሂል ያላቸዉን አሰተዋጽኦ በማነጻጸር የተሻለዉን ሞዴል መለየት በሚል ርእስ ጥናት አካሂዷል፡፡ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሳዉ ምክንያትም መምህራን የማንበብ ትምህርትን ሲያስተምሩ በመማርያ መፅሀፍ ላይ ብቻ ተመርከኩ ሲሆን እነዚያንም ምንባቦች አንዴ በመምህሩ ከተነበቡ በኋላ የተሻለ የማንበብ ችሎታ ባላቸዉ ዉስን ተማሪዎች ይነበባሉ፡፡ ሌሎች ተማሪዎች በማንበብ ትምህርት ክፍለ ጊዜ አንባቢ ሳይሆኑ አድማጮች ናቸዉ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሂደቱ የተማሪዉችን የማንበብ ፍላጎት የሚያነሳሳ የማንበብ ክሂል እንዳይዳብር እንቅፋት እንደሆኑ ከሱ በፊት በተካሄደዉ ጥናት አንብቦ አረጋግጧል ባረጋገጠዉ ጥናትም ከሁለቱ ማስተማሪያ ሞዴሎች የላይ ታች የማንበብ ክሂል ማስተማሪያ ሞዴል ለተማሪዎች አንብቦ መረዳ ችሎታቸዉ ከፍተኛ አስተዋጾ እንዳለዉ አረጋግጧል፡፡

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ጥናቶች ስንመለከት የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ በተማሪዉ የማንበብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እና ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዉ አንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋፆ እንዳለዉ አጥኚዋ ተገንዝባለች፡፡

አጥኝዋ  በምትሰራበት በእሉባቦር ዞን ሰሌ ኖኖ  በብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ማስተማር  ጊዜ ተማሪዎች አንድን ነገር አንብቦ የመረዳት ችግር ጎልቶ ማየቷ ጥናቱን እንድታጠና አነሳስቷታል፡፡

## 1.3.የጥናቱ መሪ ጥያቄዎች

ሀ. የአማርኛ መማርያ የሚቀርቡ ምንባቦች የተማሪዉን  አንብቦ የመረዳት ፍላጎትን የሚያነሳሱ  ናቸዉ?

ለ.  በአንብቦ የመረዳት ሂደት በተማሪ ተኮር እና በመመህር ተኮር የመማር ማስተማር ስልት ልዩነት አለ?

## 1.4. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ የተማሪዉ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ማዳበር አለማዳበሩን ለመለየት ነዉ፡፡

ከዚህ አጠቃላይ አላማ ላይ ለመድረስ የሚያስችሉ ዝረዝር አላማዎች  ይኖሩታል፡፡

- የአማርኛ መማርያ የሚቀርቡ ምንባቦች የተማሪዉን  አንብቦ የመረዳት ፍላጎትን የሚያነሳሱ ናቸዉ?
- ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴና በመምህር ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ መካከል የጎላ ልዩነት መኖር አለመኖሩን  ለመለየት፡፡

## 1.5. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት  የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

- ✓ ተማሪዎች  እኩል የማንበብ ችሎታ እንዲኖራቸዉ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ✓ መምህራን የተማሪዎችን የአነብቦ መረዳት ችሎታ በመገንዘብ የትምህርት እቅድ እና የንባብ ትምህርት መርሃ ግብር ሲያዘጋጁ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከማጎልበት አንጻር እንዲተገብሩ ሊረዳቸዉ ይችላል፡፡
- ✓ ተማሪዎች በራሳቸዉ ተነሳሽነት ምንባብ አንብበዉ የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉን እንዲዳብሩ ሊረዳ ይችላል፡፡
- ✓ የቋንቋ መምህራ የተማሪዉ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ  ለይተዉ በማወቅ ተመሳሳይ ጥናት እንዲያካሂዱ ሊረዳ ይችላል፡፡

- ✓ ተማሪዎች በሚያደርጉት የእለት ተእለት ተግባራቸዉ በራስ የመተማመን ችሎታቸዉን ሊገነባ/ሊያሳድግ ይችላል፡፡
- ✓ በትምህርታቸዉ ንቁ ያልሆኑ ተማሪዎች በዉይይቱ ጊዜ በቡድን ዉስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ሊረዳ ይችላል፡፡
- ✓ በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴና በመምህር ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ከተማሩ በኋላ የትኛዉ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለዉ እንዲለዩ ሊያደርግይችላል፡፡
- ✓ ጥናቱ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ከመጠቆም አንጻር ለወደፊቱ ለሚደረገዉ የስረዓተ ትምህርት ማሻሽያ ክንዉን እንደ ግባት ሆኖ ልያገለግል ይችላል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ቦታ፣ ጥናቱ የሚያተኩርባቸዉ ይዘቶች እንዲሁም በጥናቱ ውስጥ ከተካተቱት እና የመረጃ ምንጭ ከሆኑ አካላት አንጻር ወሰኑ ተለይቶ ቀርቧል፡፡በኢሉባቦር ዞን ኖኖ ሰሌ በቢርቢርሳ ወረዳ ዉስጥ ከሚገኙ የኮምቦልቻ ና የብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚያተኩረዉ በብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን በዚህ ትምህርት ቤት ዉስጥ ከ9ኛ (A-F) ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች ዉስጥ ጥናቱ ትኩረት የሚያደርገዉ በ9ኛ A ና B ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

## 1.7. የጥናቱ ዉስንነት

ጥናቱ የሚከተሉት ዉስንነቶች ይታዩበታል፡፡ይሄዉም ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉን አስተዋጽኦ ለመፈተሽ የነበረዉ የጊዜ ጥበት የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመረዳት ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን በአጥኝዋ አመለካከት በተሸለ ሁኔታ ሰፋ ያለ ጊዜ ተመድቦና ሰፊ ናሙና ተወስዶ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴን በማከናወን ምንባብን ቢማሩ ጥናቱ ይበልጥ የተሳካ ይሆን ነበር፡፡ በአጠቃላይ ጥናቱ እነዚህ ውስንነቶች የሚታዩበት በመሆኑ እንከን አልባ ነዉ ማለት አይቻልም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የንድፈ ሀሳብ ቅኝት

በዚህ ምእራፍ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉ አስተዋጾ የሚል ርእስ ሲሆን በጥናቱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ተቀራራቢነት ያላቸዉ የምሁራንን ሀሳብ ና የቀደምት ጥናታዊ ጽሁፎች በማንበብ አጥኝዋ ተመልክታለች፡፡

### 2.1.1 ተማሪ ተኮር ማስተማርያ ዘዴ ምንነት

ተማሪ ተኮር አቀራረብ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ እየተሳተፉ በሚያገኙት ትምህርት እራሳቸዉን የሚገነቡበት ነዉ፡፡ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር አቀራረብ በክፍል የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ አብዛኛዉን ጊዜ የመምህሩ ትኩረት ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና ተማሪዎች ዋነኛ የትምህርቱ ተሳታፊ በመሆን በራሳቸዉ ጥረት የሚማሩበት መንገድ ማለት ነዉ፡፡

Richards & Rodagers (2001) በተማሪ ተኮር ማሰተማር እና የትምህርት አላማዎችን በማዋሃድ በቡድኑ ዉስጥ የተነሳሽነት ስሜት መፍጠር ነዉ ይላል፡፡ በአጭሩ ተማሪ ተኮር የመማር ስነ ዘዴ መምህሩ በክፍል ዉስጥ የመማር ማስተማር ሂደቱን በማመቻቸት ተማሪዎች የተግባቦት ሂደታቸዉን እና የቋንቋ አጠቃቀም ክህሎቸዉን እንዲያዳብሩ እንደዚሁም ተነሳሽነታቸዉ ከፍ እንዲል በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ መምህር አመቻች እንደሆነና ጠቋሚ እንደሆነ ተማሪዎች ደግሞ ሁሉንም ነገር በራሳቸዉ የሚሰሩ መሆኑን ከምሁራኑ ሀሳብ እንረዳለን፡፡

Richards & Rodgers (2001) ትክክለኛ የሆኑ ተግባራት በስረዓተ ትምህርቱ ላይ የተቀመጡ የግብዓት አላማዎችን እንዲገነዘቡ ተማሪዎች በተግባቦት ሂደት ላይ እንዲሳተፉ እንዲሁም የተግባቦት ሂደት ጠቀሜታ ላይ መረጃ እንዲለዋወጡ እና የቋንቋ አጠቃቀም ብቃታቸዉ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል በማለት ያብራራሉ፡፡

በአጠቃይ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በምናስተምርበት ጊዜ ተማሪተኮር የማስተማር ስነዘዴ በክፍል ዉስጥ ተግባራዊ ቢደረግ የተማሪዎችን ተሳትፎ እና ተግባቦት አቅም በማሳደግ ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ማለት ነዉ፡፡

Johnes (2007) እንደሚያብራራዉ ለትምህርቱ ገለፃ ለሚሰሩት ትግበራ፤ ለእርማት ለምክር ወይም ለሽልማት መምህራቸዉን ሊጠብቁ ይችላሉ እንጂ የተለዩ ተግባራት ለመስራት መምህራንን ለመጠበቅ አይገደዱም፡፡ የሚሰጣቸዉን ስራዎች ለመስራት በተለያዩ የማስተማር ብለሀት እርስ በርሳቸዉ ሀሳብ በመቀባበልና በመግባባት ያከናዉናሉ፤ አንዱ ተማሪ ለሌላዉ ዋጋ ይኖረዋል፡፡ እንደ ዉይይት ክርክር ወዘተ የመማር ብልሃቶች ላይ ብቻ የመምህራንን እገዛ ይሻሉ፡፡ ስራዎቻቸዉንም በግል በጥንድ በቡድን እና ከመላዉ ክፍል ጋር ያከናዉናሉ፡፡ በአጭሩ በተማሪ ተኮር ትምህርት አቀራረብ በመማር ማስተማሩ ሂደት ዉስጥ ተማሪዎች በነጻነትና የራሳቸዉን ሀሳብ እየገለጹ በንቃት በመሳተፍ ይማራሉ፡፡

Tudor (1996) እና Mccombs (1997) የቋንቋ ትምህርት ገንቢ ሊሆን የሚችለዉ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ዉስጥ በንቃት እየተሳተፉ እዉቀታቸዉን እና እምቅ ችሎታቸዉን ከነበራቸዉ ልምድ ጋር እያዋሃዱ በራሳቸዉ ጥረት ሲማሩ ነዉ፡፡ በትምህርት ቤት ዉስጥ አንድ መምህር ከመማሪያ ክፍል ዉስጥ ከሚሰጥበት /ከሚያስተምርበት/ መምህር መራሽ ሞዴል በተቃራኒ ተማሪዎች የራሳቸዉን ትምህርት እንዲማሩ በሚያነሳሳቸዉ ትምህርት ዙሪያ ያተኮረ ነዉ ይላሉ፡፡

ተማሪ ተኮር አቀራረብ የስረአተ ትምህርት መሳርያዎች መዘጋጀት ያለባቸዉ ተማሪዎችን ማእከል ባደረገ እና ፍላጎታቸዉን ጠብቆ ተግባራቱን በራሳቸዉ እዉቀት መማር እንዲችሉ ተደርገዉ መቅረብ አለባቸዉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን ካዘጋጀን በኋላ ተማሪ-ተኮር ትምህርት በምናከናዉንበት ጊዜ የተለያዩ ምክንያቶች ላይ በመመስረት የተለያዩ ክንዉኖችን ማከናወን አለብን፤ ክንዉኖቹም የቡድን ስራዎች የችግር አፈታት ጥያቄን ያጠቃልላል ይላል፡፡

ተማሪ ተኮር ትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች ዉይይት፣ የቡድን ስራ ማካተት አለበት ይላል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ቋንቋን ማስተማር የተለያዩ ጥቅሞች እንዳሉት የተለያዩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ከጥቅሞችም ዉስጥ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች እንደሚያዳብር ገልጸዋል፡፡ ከክሂሎች ዉስጥም አንዱ ምንባብ ነዉ፡፡

ተማሪ ተኮር አቀራረብ ትምህርቱ ሲቀርብ በመማር ማስተማሩ ሂደት ዉስጥ በነጻነት የራሳቸዉን ሀሳብ እየገለጹ በንቃት በመሳተፍ ይማራሉ፡፡ በተማሪ ተኮር አቀራረብ ቋንቋን ማስተማር ተለያዩ ፊይዳዎች እንዳሉት የተለያዩ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ለምሳሌ እንደ Waticness et al. (2007) በአዕምሮአዊ ብቃት ማለትም በንቃት ማሰብን፣ የቀደመ እዉቀትን መገንባትን እና አዲስ ስያሜዎችን ማምጣትን ከባህሪ አንጻር በንቃት መስራትን እና ነገሮችን አስተዉሎ ማከናወንን፣ ከማህበራዊ መስተጋብር አንጻር ደግሞ ከሌሎች ጋር ተባብሮ መስራትን እና መተጋገዝን ያካትታል፡፡

ከዚህ የምንረዳዉ ተማሪተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ በትምህርት ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ ሒዎት ዉስጥም ከሳች ጋር ንዴጽ መስማማት ንደምንችል በማህበረሰቡ ዉስጥ ሀላፊነት በመዉሰድ መስራት እደምንችል እንረዳለን፡፡

እንደ Xiaomei (2010) ማብራሪያ ተማሪዎች የራሳቸዉን ልምድና የቀደመ እዉቀት በመጠቀም በጥረታቸዉ በመማር ማስተማር ሂደት በንቃት ተሳትፈዉ የሚያገኙት ነዉ፡፡ በዚህ መንገድ እየተሳተፉ ለመማር እንዲችሉ መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህም የትምህርት ግብዓት የሚገኘዉ የሚቀርቡላቸዉ ይዘቶች በተማሪ ተኮር አቀራረብ የሚሰጡ ከሆነ ብቻ ነዉ፡፡ ስለዚህ መምህራን የቋንቋ ትምህርቱን ሲያቀርቡ ተማሪዎች በራሳቸዉ ጥረት እዉቀት የሚገበዩበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት እንዲሳተፉበት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.1.2. የተማሪ ተኮር አቀራረብ መርሆች

የተማሪ ተኮር አቀራረብ የራሱ መርሆች አሉት። መርህ ማለት የተማሪ ተኮር አቀራረብን በስራ ላይ ማዋል መምህራንና ተማሪዎች ማወቅ የሚገባቸዉ የተግባራት መፈፀሚያ ስልቶችን የሚያሳይ ፅንሰ ሀሳብ ነው። እነዚህም መርሆች Brandss & Ginnis (1986) እንደሚከተለዉ ገልጸዋል::

1. ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ተሳትፎ ማድረጋቸዉ አስፈላጊ ነዉ። ይህ ሙሉ ለሙሉ የዉጫዊ ግበዓት ጫና ሳያስፈልግ ዉስጣዊ ችሎታቸዉ መማር እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ ይህ ማለት መምህራን ሁኔታዎችን ማመቻቸት ብቻ ተማሪዎቹ በመር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ተሳታፊ ሆነዉ እዉቀት የሚገኙበት በመሆኑ ተግባራዊነትን ያረጋግጣል ማለት ነዉ። ይሁን እንጂ ተማሪዎች ዉስጣዊ ችሎታ ቢኖራቸዉም ካደጉበት ማህረራዊ፣ ባህላዊ ሁኔታዎች አንፃር ደግሞ አቅጣጫን ለማመልከት እገዛ ያስፈልጋቸዋል፡፡ መምህራን እገዛ ሲያደረጉ ተማሪዎች ካደጉበት ማህበራዊ ባህላዊ ልምድ አንፃር መተግበር ይኖርባቸዋ።ይህ ማለት ምንም እንኳን ተማሪዉ በራሱ ችሎታ መማር እድል መሰጠቱ ተገቢ ቢሆንም ተመሪዉ ያደገበት ማህበረሰብ ያለዉን ባህል መርሳት የለበትም ማለት ነዉ።

2. ተማሪዎች በትምህርቱ ይዘት ዉስጥ ሙሉ ሀላፊነት ይዘዉ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል። ይህም ተማሪዎቹ በትምህርት ሂደት ዉስጥ ተሳታፊ በመሆን እራሳቸዉ ስለሚማሩ ተማሪዎች እርስ በርስ በሚያደርጉት መሰተጋብረ መሳተፍ እዉቀት የሚያደራጁበት ሁኔታ ነዉ።
3. ትምህርት አግባብ የሚኖረዉ ተማሪዎቹ ለሚማሩት ነገር ፍቺ በመስጠት ከተገነዘቡ፡ በስርዓተ ትምህርት መረጣዉስጥ ከተሳተፉ፡ የመማር ማስተማር አላማዎች በችላታቸዉ በመምረጥ፡ በመግልፅና በሚያስፈልጉት ነገሮች ዉስጥ የመቀበል ሁኔታን ከገለፁነዉ።
4. መምህራን ለመማርማስተምሩ ሂደት ሁኔታዎችን የሚያመቻቹና በትምህርት መረጃነት የሚያገለግሉ ናቸዉ። በመሆኑም መምህራን ለተማሪዎች እዉቀት አስተላላፊዎች ሳይሆኑ ተማሪዎች እርስ በራሳቸዉ እንዲማማሩ ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ና ፍንጭ ሰጪ ሁነዉ መቅረብ አለባቸዉ።

5. ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት ከልምዳቸዉና ካላቸዉ የእዉቀት ደረጃ ጋር ማዛመድ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 2.1.2. የንባብ ብያኔ

ንባብ አንዳንድ ሰዎች የንባብ ድርጊትን ለመቆጣጠር ቀላል ስራነዉ ይላሉ ነገር ግን ብዙ የተለያዩ ችሎታዎችን የሚስብ ዉስብስብ ሂደት ነዉ፡፡ ማንበብ የተጻፈዉን የጽሁፍ ሀሳብ ለሌሎች የማስተላለፍ ነዉ፡፡

የማንበብ ክሂል በዉስጡ የንባብ ክሂሎችን የያዘ ነዉ፡፡ ከክሂሎችም ዉስጥ አንዱ የኣንብቦ መረዳት ክሂል ነዉ፡፡ ተማሪዎች ብዙ ጊዜ የሚያነቡ ከሆነ ንባብን የመረዳት ችሎታቸዉ ይዳብራል ይላል (Fry 1963)::

Pirson (2009) በምንባብ ትምህርት ላይ የተደረጉት ለዉጦች ይበልጥ መረዳትን መሰረት ያደረጉ የትምህርት አቀራረቦች ተግባራዊ እያደረጉ በመሄዳቸዉ አንድን ጽሁፍ ድምጽን በመጠቀም በፍጥነትና በማራኪ አገላለጽ ማንበብ ወይም ቃላዊ ትኩረት መሆን ቀርቶ ግንዛቤያዊ አቀላጥፎ ማንበብ በቦታዉ እንደ ተተካ ገልጿል፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳዉ በምንባብ ትምህርት የተደረጉ ማሻሻያዎች አንድን ነገር አንብቦ ለመረዳት ከፍተኛ ጥረት እንዳደረገ እንረዳለን፡፡

Anderson (1999) ይሄንን ሀሳብ ሲያጠናክረዉ በቂየሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያነበቡትን ጽሁፍ በብቃት መረዳት እና ማስታዎስ ብቻ ሳይሆን በተቻለ መጠን በጥሩ ፍጥነት አንብቦ መረዳትንም የሚያጠቃልል መሆኑን ገልጽዋል››በመቀጠል የንባብ ኪሂል ትምህርት አንብቦ መረዳትን ለማዳበር አስፈለጊ ሲሆን ምንባብ ሂዎት አለዉ ብለን የምናስበዉ ተማሪዉ ለዚህ ስኬት የሚያደርገዉ ጉዞ ዉስጥ የሚያገኘዉ ዉጤት ነዉ ይላሉ Dole & Duffy (1992):: እንዲሁም Harmer (2001) ማንበብ ከመቀበል ኪሂል አንዱ ሲሆን ከጽሁፍ ዉስጥ ፍሬ ሀሳብ ለይቶ ማዉጣት፤ የጽሁፍን አጠቃላይ ሀሳብ መረዳት ፤የጽሁፈ ፍሰትን ማዎቅ ፤ የአንቀጽ አወቃቀርና አደረጃጀትን ማወቅ፤የቃላት አዉዳዊ ፍችዎችን መገንዘብ አንደሆነ ይገልጻል፡፡ ልጆች የበለጠ ብቃት ያላቸዉ አንባቢያን ለመሆን የንባብ ፍቅርን ለማሳደግ ከመፅሃፍ ጋር ስኬታማ የንባብ ልምዶች ሊኖራቸዉ ይገባል፡፡

አንባቢዎች የግለሰቦችን ቃል ለመለየት የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማ ከሚጠቀምባቸዉ የመረጃ ምንጮች ጋር የሚዛመዱ ሶስት የንባብ መቃኛ ስረአቶች አሉ እነሱም፡-ትርጉም አወቃቀር እና የመረጃ እይታ ናቸዉ፡፡

Davis (1995) ማንበብ ግላዊ የአይምሮ ግንዛቤ ሂደት ሲሆን አንባቢዉ ጸሐፊዉ በጽሁፍ ሊያስተላልፍ የፈለገዉን መልእክት አንብቦ ለመረዳት የሚተጋበት ነዉ፡፡ ይህ ማለት አንባቢዉ በግሉ ተነሳስቶ የሚተገብረዉ እንጂ በሌሎች ሲነበበ የሚያዳምጠዉ/ሌሎች እንዲረዱት ጮክ ብሎ የሚያነበዉ ተግባር መሆን እንደሌለበት ነዉ፡፡

እንግዳ (1992) Higgins (1984) ዋቢ አድርጎ ማንበብ ዓላማ መወሰንን፣ የምንባቡን መልእክት አስቀድሞ መገመትን፣ የተገመተዉን ግምት ማጣራትን እና የምንባቡን መልእክት ከግል ገጠመኝ ጋር አዛምዶ ተቀባይነቱን /ተጨባጭነቱን መገምገምን የሚያጠቃልል ተግባር ነዉ፡፡በማለት ገልጸዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ምንባቡን ከማንበባችን በፊት የምንባቡ መልእክት ምን ሊሆን እንደሚችል መገመትን የሚጠይቅ ፣ በምናነብበት ጊዜ ደግሞ የግምታችን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እነደሆነ ነው፡፡

Nilsn (1963) ንባብ በየእለቱ በሚደረግ ተከታታይነት ያለዉ ልምምድ እያደገና እየጎለበተ የሚመጣ ክሂል መሆኑን ገልጸዉ ለተማሪዎች ያለዉን ጠቀሜታ ሲያስረዱ ንባብ በተማሪዎች ዉጤት ላይ በየጊዜዉ የሚታይ ጥቅም ያለዉ የቋንቋ ክህል ነዉ፡፡ በተጨማሪም የንባብ ልምድ ተማሪዉች ከዚህ በፊት እና ለአሁኑ ም ሆነ ለወደፊት ለንባብ ስራቸዉ መሰረታዊ የሆነ እዉቀት የሚሰጥ ነዉ ይላሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ተማሪዉም ሆነ ማንኛዉም ሰዉ አንድን ነገር ለማወቅም ሆነ ለመረዳት ማንበብ እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ለተማሪዎችም ደግሞ ጥሩ ዉጤት ለማስመስገብና እዉቀት ለማግኘት ማንበብ አስፈላጊ መሆኑን ነዉ፡፡

Wallace (1992: 4) ማንበብ አንባቢዉ ከፀሐፊዉ ጋርግንኙነት ለመፍጠር የፀሐፊዉን ሀሳብ ለመረዳት እና ለመተርጎም በግሉ የሚያደርገዉ ጥረት ነዉ፡፡ ሀሳብ ተረድቶ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳዉ ማንበብ አንባቢዉን እና ጸሐፊዉን የሚያገናኝ መሆኑን ነዉ እናም አነባቢዉ የጸሐፊዉን ሀሳብ ተረድቶ በራሱ አገላለፅ እንዲተረጎም የሚያስችለዉ መሳሪያ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

Williams (1984: 3) ማንበብ ተፈላጊዉን መረጃ የማግኘትና የመረዳት ሒደት ነዉ፡፡ የመረዳቱ ሁኔታ ከሚነበቡት አላማ የማንበብያ ስልት የተለየሊሆን ይችላል፡፡

Grellete (1981: 3) በተመሳሳይ መልኩ የአነባብ ስልትን መለያት ሲያስቀምጡ ‹‹ከማስታወቅያ ፍሬ ሀሳቡ በገረፍታ የሚነበብ ሲሆን ሳይነሳዊ ምርምር ግን በጥልቅ ማንበብን ይጠይቃል›› ከዚህ የምንረዳዉ የአነባብ ስልታችን ለንባቡ ያለን ትኩረት የተለያየ ልሆን እንደሚችል ነዉ፡፡

ምንባብን በክፍል ዉስጥ ስናስተምር የቃላትን አነባብ፣ የተዋጣለት የንግግርና የሀሳብ አገላለፅን፣ ጥራት ያለዉ የአነባብ ድምፀትን፣ሀሳብን ከጽሁፍ እንድረዱ የማድረግ ሁኔታዎችን ሁሉ ሊያተቃልል እንደሚችል Nutall (1982፡ 2) ይገልጣሉ፡፡ በዚህ ዉስብስብ ባህሪዉ የተነሳ ንባብ አንድ ወጥ ብያኔ እንዳይኖረዉ አድረጎታል በማለት ተስፋዬ (2006፡ 6) ይገልፃሉ፡፡ ነገር ግን አብዛኛዎቹ ብያኔዎች ማእከል ባደረገ መልኩ Harmer (1991፡ 190) ‹‹ንባብ በአይን እና በአይምሮ የነቃ እንቅስቃሴ የሚያከናዉን ተግባር ሲሆን፣ አይን ከወረቀቱ መልእክትን ይቀበላል፣ አይምሮ ደግሞ የተቀበለዉን መልእክት ከጥቅም ላይ ያዉላል›› በማለት ይገልጹታል፡፡ ከዚህ ብያኔ የምንገነዘበዉ ምንባብ የተጻፈን መመልከት ብቻ ሳይሆን መረዳትም ጭምር እንደሆነ እንረዳለን፡፡ እንዲሁም Grellet (1982፡ 4) ከንባብ ጠቀሜታዎች መካከል መረጃን መግኘትና መዚናናት ዋናዋና ዎቹ አላማዎች ቢሆኑም የሚነበበዉን ነገር መገንዘብ ግን የንባብ ዋና ጉዳይ ነዉ በማለት ይገልፃሉ፡፡ ምንባብ እደየተማሪዉ የክፍል ደረጃ በይዘትና አቀራረቡ ተመጥኖ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡በመሆኑም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚገኙ ተማሪዎች ምንባብ አንብቦ መረዳት በሚል መልክ ይሰጣል፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ለምንባብ ከሰጡት ብያኔ የምንረዳዉ ማንበብ የሚነበበዉን ነገር መምረጥ መገምገም በጽሑፍ የተቀመጡትን መልእክቶች እያስተዋሉ ተጨባጭ የሆኑ ፅንሰ ሀሳቦችን ከራስ ገጠመኝ ጋር ማገናዘብን የሚጠይቅ ክሂል መሆኑን እንረዳለን፡፡

አንድን ጽሁፍ ለማንበብ የንባብ ችሎታ መዳበር ወሳኝ ሲሆን በመማር ማስተማር ሂደት ቤትኛዉም የትምህርት ሁኔታ አንድን ነገር ለመረዳትም ሆነ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አንብቦ መረዳትን መቻል አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ ምሁራኑ አክለዉ በተለይ አሁን ካለንበት ዘመን መረጃን ከድህረ ገጽ ከመጽሄትእና ከተለያዩ መጸሃፍት አንብቦ መረዳት እንዲሁም ምላሽለመስጠት የተማሪዎች የማንበብ ክህሎት እና ብለሀት በተማሪዎች ዉጠት ላይ ትልቅ ሚና እንዳለዉ ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም እንደ Hedge (2000) አገላለጽ አእምሮአዊ ብልሀቶች ቀጥተኛ የቋንቋ መማር ብለሃት ሲሆኑ ተማሪዎች በንቃት ከታላሚዉ ቋንቋ መልእክቶችን እንዲቀበሉ እና እንዲያፈልቁ ያስችላሉ፡፡ ስለሆነም በአይምሮአዊ በልሀት እርዳታ አመካይነት ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች ከአዲሱ መረጃ ጋር መገናኘት እንዲችሉ እና አእምሮአዊ ብልሀቶችን በመጠቀም የተማሪዎችን የንባበ ግንዛቤ ማዳበር እንደሚቻል Bakere & Brown (2007) ያስረዳሉ፡፡ ይህም ልእለ-አእምሮአዊን ከሁለት ነገሮች አንጻር መመልከት እንደሚቻል ሲያመለክት የመጀመርያዉ ከግለሰቡ ችሎታ፣ ከስራዉ ጋር የተገናኘ የስራ ጥንካሬ እና ድክመት ለመረዳት ሚያስችል ሲሆን ሁለተኛዉ ደግሞ የአንድን ተግባር አሰራር መቆጣጠር እና በመረጃ አሰባሰብ ሂደት ዉስጥ ብዙዉን ጊዜ የተለየ ተግባር ተብሎ የሚጠራዉን የማቀድ፣ የመቆጣጠር እና የመገምገም ብለሀቶችን መተግበርን እንደሚያካትት ይገልጻሉ፡፡

### 2.1.3. የንባብ አይነቶች

#### 2.1.3.1. የፍጥነት ንባብ

የፍጥነት ንባብ ማለት አንድ አንባቢ ከተጻፉት ጽሁፎች ላይ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ ያነባል የሚል ማለት ሲሆን የንባብ ፍጥነት የሚለካዉ በደቂቃ ዉስጥ በምናከናዉነዉ የቃል ብዛት ይሆናል ይላል፡፡ Natal (1982) ከዝቅተኛ አንባቢያን ፈጣን አንባቢያን የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ ከፈተኛ ነዉ፡፡ ተማሪዎች የንባብ ፍጥነት እንዲኖራቸዉ ደጋግመዉ ማንበብ አለባቸዉ፡፡ ፈጣን አንባቢያን በአንድ በተጻፈ ነገር ላይ ያለዉን ቃል እየቆጠሩ ሳይሆን አያይዘዉና አከታትለዉ ስለሚያነቡ የሀሳብ መቆራረጥ ችግር አያጋጥማቸዉም ይሄም የተሟላ ሀሳብ ለመያዝ ያግዛቸዋል በመሆኑም የመረዳት አቅማቸዉ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ከዚህ ምሁር አባባል የምንረዳዉ አቀላጥፎ ማንበብ ሀሳብ ሳይቆራረጥ ማንበብ የምንችልበት የንባብ አይነት መሆኑን እንረዳለን፡፡

አቀላጥፎ ማንበብ ለአንብቦ መረዳት ጠቃሚ በመሆኑ ተማሪዎች መሰረታዊ ሆኑ የአቀላጥፎ ማንበብ ልቶችና ክሀሎችን መማራቸዉ በደንብ መረዳታቸዉ በንባብ ስክታቸዉላይ አዉንታዊ ተጽኖ ይኖራቸዋል፡፡ Piaget (2011) ከምንባብ ጋር የሚታገሉ ተማሪዎች ቀልጣፋ አንባቢ አይደሉም፤ ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ ዝቅተኛ ነዉ ማለት ነዉ ይላሉ፡፡

ስለዚህ ከዚህ የምንረዳዉ አቀላጥፎ ማንበብ ስልቶችን ማስተማር የንባብ ክሂሎችን በማሳወቅ የአንብቦ መረዳት ችሎታን ያሳድጋል፡፡ አንብቦ መረዳት ችሎታ በአቀላጥፎ ማንበብ ላይ

የተመሰረተ በመሆኑ ተማሪዎች የአቀላጥፎ ማንበብ ስልቶችን ማወቅ አለባቸዉ ሲሉ Young, & Rasiniski (2009) ያስረዳሉ።

Kuhan et al. (2015) ፍጥነትን ሲገልጹ አንባቢዉ በጽሁፍ ዉስጥ የቀረቡትን ቃለት ለመለየት ከሚያደርገዉ ትግል ተላቆ ዘና ባለ አቀራረብ በእይታ ብቻ ቃላቱን በፍጥነት የማንበብ ብቃት ነዉ ይላሉ። ከአቀላጥፎ ማንበብ አንጻር ፍጥነትን ለመመዘንበቀረበዉ መሰረት ብዙን ጊዜ ጥቅም ላይ የሚዉለዉ መለኪያ ምን ያህል ቃላት በደቂቃ እንደተነበቡ በትክክል በመቁጠር ዘዴ የሚከናወን ነዉ (Tiroglen & Hudson 2006)::

### 2.1.3.2. የዝግታ ንባብ

የዝግታ ንባብበቃላት በሀረጋት በአረፍተነገሮችዉስጥ ያለን ሀሳብ ወይም የጽሁፍን ፍላጎት ስሜት የመለየት ችሎታ ነዉ። ይህም ካለበት አዉድ በመነሳት የሚቀጥለዉን መተን በይን ያካትታልለማንበኛዉም የስነ ጽሁፍ ጥናት አስፈላጊ ነዉ እና ይህ የአነባብ ስልት የግለሰቦችን ጽሁፍ የምንረዳበት የአነባብ ስልት ነዉ።

### 2.1.3.3. ሰፊንባብ

ሰፊ ንባብ ማለት አንባቢዉ የንባቡን ችሎታ የሚያሳድግበት እንዲሁም በአለም ላይ ያሉ ባህሎችን እመነቶች የሚረዳበት የንባብ ስልት ነዉ። እንዲሁም አዲስ አዉቀትን የሚገነቡበት በእዉቀት ላይ እዉቀትን ለመጨመር የሚካሄድ የንባብ ስልት ነዉ ይላል Rechard (2000)።

### 2.1.3.4. ጥልቅ ንባብ

አንደ Berllet (1981) ጥልቅ ንባብ ማለት አጫጭር ምንባቦችን በማንበብ ከምንባቡ የተወሰነ መረጃ ለማግኘት የሚደረግ የአነባብ ስልት ነዉ። Eta (1991) ይሄንኑ ሲያብራራ የጥልቅ ንባብ መለያዉ ለየት ባለ ትኩረት በጥንቃቄ የሚተገበር መሆኑ ነዉ። በተወሰነ ርእስ ዙርያ የቀረቡትን ጉዳዮች መለየት እንድንችል የሚረዳን የንባብ ስልት ነዉ።

## 2.1.4. የንባብ ትምህርት አስፈላጊነት

ራስን ከዘመኑ አዳዲስ ነገሮች ጋር አጣጥሞ ለመኖርየማንበብ ክሂል ከፍተኛ ሚና አለዉ። የንባብ ትምህርት ለሁለት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋል እነዚህም የሚከተሉት ናቸዉ።

1. ተማሪዎችን በሕወት ዘመናቸዉሊያነቧቸዉ በሚፈልጓቸዉንባብ ልቦለድ ግጥም ወቅታዊ ነገሮች ጋር ለማስተዋወቅ እናለማለማመድ።

2. እነዚህን ግጥም ልቦለድ በተሳካ ሁኔታ ማንበብ የሚችሉበት ዘዴ ለተማሪዎች ለማሳወቅ ነዉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን የሚያነቡትንም ንባብ የአነባብ ቴክኒክ ጭምር ለማስተማር ስለሚያግዝ ነዉ፡፡

### 2.1.5. የንባብ ትምህርት አቀራረብ

መምህር ለተማሪዎች የክፍለ ጊዘዉን ትምህርት ርእስና አላማ ያስተዋዉቃል፡፡ የቀረቡትን ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ይጠይቃል ምንባቡን ተማሪዎች በርጋታ እንዲያነቡት ያደርጋል፡፡ የምንባቡን አንዳንድ አንቀፅ ካነበቡ በኋለ ምንባቡን በማስቆም በአንደኛዉ አንቀፅ ዉስጥ የተዱትን ሀሳብ እንዲገልፁ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ምንባቡን ጨርሰዉ እንዲያነቡ ካደረገ በኋላ በምንባቡ መልእክት ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ይጠቁማል፡፡ ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለሚሰጡ ፈተናዎችም ሆነ መልመጃዎች በጥሩ ሁኔታ (በማብራራት) እንዲሰሩ ያነሳሳል፡፡

ማንበብን ስናስተምር ከጽሁፍ ሀሳብ  አስተያየት ስሜት አና አጠቃላይ መልእከቱን ከመተርጎም እና ከመረዳት ጋር አያይዞ መሆን አለበት፡፡ እንዲሁም ማንበብን የሚያስተምር መምህር በፅሁፍ የሚቀርብ ሀሳብ ና በንግግር የሚቀርብዉ የተለያዩ እንደሆኑ በመጀመርያ ለተማሪዎች ማሳወቅ አለበት፡፡ ንባብን በምናከናወንበት ጊዜ ሶስት ሂደቶችን ማከናዎን አለብን፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ ቅድመ ንባብ፣ በንባብ ላይ እና ድህረ ምንባብ ናቸዉ፡፡

#### 2.1.5.1. ቅድመ ንባብ

የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በክፍል ዉስጥ የማስተማር ሂደት ጊዜ በቅድምያ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት በማነቃቃት ይጀምራል በማለት Williams (1984፡ 36) ይገልጻሉ፡፡ መምህሩ ምንባቡን ከማስነበቡ በፊት ተማሪዎችን የማነቃቃቱ ቅድመ ምንባብ ተግባትን ማከናወኑ ተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ከመቀስቀሱ ባሻገር ተማሪዎች ስለሚያነቡት ነገር ቅድመ ትንብያ እና የአይምሮ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያስቸላቸዋል፡፡ ነገር ግን መምህሩ ይህን ያህል የማነሳሳት እና የማስተዋወቅ ችሎታ ቢኖረዉም በአንድ ምንባብ የሁሉንም ተማሪዎች ስሜት እና ፍላጎት መገንዘብ አይቻልም፡፡

ከዚህ ምንረዳዉ ስለ ምንባቡ ርእስ  ያለንን ቅድመ ንባብ እዉቀት እንዲ ሊሆን ይችላል በማለት መልስ የምሰጥበት ወይም እንዲህ ሊሆን ይችላል በማለት ጥያቄ የሚያስከትል የንባብ ሂደት ነዉ፡፡ በዚን ሰዓት መምህሩ ቅድመ ትንብያዉን እንድንሰጥ አነቃቂ ይሆናል ማለት ነዉ

### 2.1.5.2. የንባብ ጊዜ

የንባብ ጊዜ የሚባለዉ ንባቡን በጸጥታና በየግላቸዉ የሚያነቡበት ጊዜነዉ በቡድንም ስለርእሱ ጉዳይ ስለ ርእሱ አላማ ከምንባቡ ከወጡት ጥያቄዎች ለይ የሚወያዩበት ጊዜ ነዉ፡፡

ይህ ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የንባብ ትምህርት አለማዎችን በተለያዩ ስልቶች አማካይነት የምናለማምድበት ነዉ፡፡ እንዲሁም አእምሮአዊ ክህላቸዉን እንዲያዳብሩ መልመጃዎችን የምንሰጥበት ከንባብ ክንዉን አንዱ ክፍል ነዉ፡፡ በንባብ ጊዜ የሚከናወኑ ክንዉኖች

- አንብበዉ የምንባቡን ዋና ሀሳብ እንዲለዩ ማድረግ
- አንብበዉ ዝርዝር ሃሳቦችን እንዲለዩ ማድረግ

### 2.1.5.3. ከንባብ በኋላ

ተማሪዎች ስለተጻፈዉ ነገር ማስተካከያ የሚሰጡበት እናየተጻፋን ነገር በመረዳት ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ የምሰጡበት ደረጃ ነዉ፡፡ እንዲሁም ላነበቡት ነገር እዉቀት የሚገበዩበት መሆኑን Green-hoad (1988) ይገልጻል፡፡ እንዲሁም የገኙትን እዉቀት ለሌላዉ የሚያጋሩበት ነዉ፡፡ ከዚህም ክንዉን በኋላ ካነበቡት ምንባብ ጋር በተያያ የተለያዩ ቀጣይ ተግባራትን የሚያከናዉኑበት ጊዜ ነዉ፡፡ በዚህ ደረጃ ተማሪዎች ለመልስ እርማት ያገኛሉ፡፡

አንብበዉ በተረዱት ነገር ላይ የፅሁፍ አስተያየት፡ ትችት ወይም ድጋፍ መስጠት የሚችሉበት ደረጃ ነዉ፡፡ ድህረ ንባበ አራት ሁኔታዎችን ከግብ ለማድረስ የሚሰጡ መልመጃዎች ሊኖሩ ይገባል፡፡ እነሱም

- አስተያየት የመስጠት ችሎታቸዉ እንዲዳብር የሚረዱ፡፡
- ካነበቡት ምንባብ አንጻር መገምገም እንዲችሉ የሚያደርግ፡፡
- አከባብያቸዉን በዚያሁኔታ ዉስጥ አስቀምጠዉ እንዲመረምሩ የሚያስችል፡፡
- የንባብ ክህልን ከሌሎች የቋንቋ ክህሎች ጋር ለማጣመር የሚያስችሉ ተግባራትን እንዲያከናዉኑ የሚያደርጉ መልመጃዎችን መስጠት፡፡

### 2.1.6. የአንብቦ መረዳት ምንነት

አንብቦ መረዳት ማለት በጽሁፍ ዉስጥ እንዲተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነዉ፡፡ አንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳትን ለመመዘን

የሚያገለግለዉ ዋና መሳርያ የአንብቦ መረዳት ችሎታ መለኪያ ፈተና ነዉ፡፡ Smith (1985) በበኩላቸዉ አንብቦ መረዳት አንባቢዉ ቀድሞ ይዞ ለተነሳቸዉ ጥያቄ መልስ ማግኛ ማለት ነዉ ይላል እንዲሁም አለም (1991) አንብቦ መረዳት ማለት ከአንድ አሀድ ዉስጥ ተፈላጊዉን መረጃ በችሎታ መሰብሰብ መቻል ማለት ነዉ፡፡

William (1983) የንባብ ትምህርቱ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያስችል ዘንድ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ እነሱም አንባቢዉ፤ ጽሁፉ እና የተለያዩተ ተግባራት ናቸዉ በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም Hocket (1956) አንብቦ መረዳት ከአንድ ጽሁፍ ዉስጥ የምንፈልገዉን ነገር መርጠን በማዉጣት ትርጉም መስጠት/መረዳት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

አንብቦ መረዳት በትምህርተ ቤት ዉስጥ ለሚደረገዉ ለነባብ ክህል አስፈላጊ ነዉ፡፡ (Pearson et al. 1992) ጥሩ አንባቢ የምንላቸዉ በሚያነቡት ፅሁፍ ዉስጥ ክህሎችን ማዳበር የሚችሉ፣ የተለያዩ ክህሎችን ለማዳበር የሚረዱብላሃቶችን የሚያነቡበትን አላማ የሚገነዘቡ፣ የደራሲዉን አላማ የሚረዱ እና በንባብ ክሂል ያገኙትን አዲስ መረጃ ከቀደመ እዉቀታቸዉ ጋር አስማምተዉ ጉዳዩን የሚገነዘቡ ናቸዉ፡፡

አንብቦ መረዳት አንባቢዉ በሚጠቀምባቸዉ የተለያዩ ብለሃቶች ይወሰናል፡፡ለምሳል የቀደመ እዉቀትን አዲስ ለሚገኝ እዉቀት ማዘጋጀት፣ መጠየቅ፣ ማጠቃለል፣ መረጃዎችን በትክክል መሰደር፣ዋና ሀሳቦችን መለየት፣መተንበይ ራስን መገምገምእና ትረጉም መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

Nattall (1996) አንብቦ መረዳት የፅሁፍን ቅደም ተከተላዊ፣ የዓረፍተ ነገሮችን የሀሳብ ግንኙነት የሚፈጥሩ አያያዦች እና የፀሀፍዉ ሀሳብ የሚንፀባረቅባቸዉ በመሆናቸዉ ትኩረት ሊሰጥባቸዉ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም Grelle (1990) ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ አንብበዉ ለመረዳት ከተለያዩ የአደረጃጀት ዘዴዎች ጋር መተዋወቅ አለባቸዉ፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ፅሁፉን ለማንበብ በሚዘጋጁበት ጊዜ የፅሀፉን አደረጃጀት በመለየት ምንአይነት የንባብ ብለሀት መጠቀም እንደሚኖርባቸዉ እንዲሁም በንባብ ሂደታቸዉ ምን አይነት ታሪክ ወይም ሀሳብ ሊመጣ እንደሚችል መገመት አንዲችሉ እንደሚያደርጋቸዉ ያስረዳሉ፡፡

አስቴር (2010) አንብቦ መረዳት ለትምህርት እድገት መሰረታዊ ሆነ ክሂል ቢሆንም አብዛኛዉ እቶጵያዊ ተማሪ ማንበብን እንደ ከባድ ስራ አድርጎ ሲያየዉ ይስተዋላል፡፡ በተለይም Wainer & Piper (2010)ን ጠቅሰዉ እንደገለጹት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የሁለተኛ እና የሶስተኛ ክፍል ተማሪዎችን ወስደዉ ባጠኑት ጥናት የንባብ ችሎታቸዉ በአማካይ ከ50 በታች መሆኑ ችግሩን ግልፅ አድረጎ ያሳያል በማለት ያብራራሉ፡፡

Campbell et al. (2001) እንዳብራሩት ማንበብ በመጀመርያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ለተማሪዎች ከሚያስፈልጓቸዉና እጅግ በጣም ከሚጠቅሟቸዉ ክህሎች አንዱ ነዉ፡፡ የማንበብ ክህል ለፈጠራና ለግላዊ እድገት ጠቀሜታ ስላለዉ በመጀመሪያዎቹ የትምህርት ደረጃዎች ከማንኛዉም ክሂል በበለጠ ትኩረት የሚስፈልነዉ፡፡ እንዲሁም ታዳጊ ህጻናት በማህበረሰባቸዉ ዉስጥ ወይም ብፍዉ ህብረተሰብ ዉስጥ የተሳትፎ ችሎታቸዉን እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ዝግጅታቸዉም ይቸምራል ይላል፤ ከዚህ የምንገነዘበዉ ማንበብ በትምህርት ለይ ክፍል እያሉ ሳይሆን ከታችክፍል እያሉ ማንበብ እነዳለባቸዉ እና በማንበብ እዉቀት በመቸበጥ አንድን ነገር ፈጣሪ እንድንሆን ማድረጉን እንረዳለን፡፡

በሌላ አገላለጽ በቅድመ ትምህርት ጊዜ ወላጆች ለልጆቻቸዉ በቤት ዉስጥ ሊያዳብሩት የሚገባ በመጀመርያ ደረጃ የሚያስፈልግ ክሂል ነዉ፡፡ የአንብቦ መረዳትን ምንነት በተመለከተ ምሁራን የየራሳቸዉን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ አንብቦ መረዳት ማለት አንባቢዉ በተገቢዉ ፍጥነት የሚፈልገዉን መረጃ የሚለይበት ተራ ያል ሆነ ጥልቅ ግንዛቤን ሚመለከት ነዉ፡፡ Wiliams (1990) እና Grellete 1981) በበኩላቸዉ አንብቦ መረዳት ማለት ከሚነበበዉ ጽሁፍ ዉስጥ አንባቢዉ ወይም ተማሪዉ እስከሚችለዉ ድረስ በብቃት የሚፈልገዉን መረጃ ማዉጣት መቻል ማለት ነዉ በማለት ገልጸዋል፡፡

Snow & Sweet (200) እና Chair (2002) አንብቦ መረዳት ከአንድ ፅሁፍ ዉስጥ የምንፈልገዉን መርጠን በማዉጣት ትርጉም መስጠት ወይም መረዳት እንደሆነ ሲያስረዱ Sheng (2000) እና Grellet (1990) እንደሚያብራሩት አንብቦ መረዳት በአንባቢዉ እና በጸሀፊዉ መካከል የሚደረግ መስተጋብር ስለሆነ በሁለቱ መንገድ ከፍሎ ማየት እንደ ሚቻል ችናአንደኛዉ በምንባቡ ዉስጥ በግልጽ የሰፈሩ ጉዳዮችንእና በጽሁፍ ዉስጥ በግልፅ ዋና ዋና ሀሳቦችን መረዳት ሲሆን፣ሁለተኛዉ ደግሞ ተጠየቃዊ እዉቀትን እና ግምትን በመጠቀም በፅሁፍ ዉስጥ በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

አንብቦ መረዳትን በክፍል ዉስጥ በመጀመርያ መምህሩ ምንባብን አንብቦ እና እንዴት ማስተማር እንዳለበት እቅድ ነድፎ ወደ መማርያ ክፍል መሄድ እንዳለበት Nuttall (1982፡ 1) ይገልጻሉ፡፡ የቅድም ንባብ ተግባራት፣ የየንባብ ጊዜ ተግባራት ችናድህረ ንባብ ተግባራት በሚሉ ሂደቶች መከፋፈል እንዳለበት Nattall (1982)፣ Williams (1984) እና Wllace (1992) ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ የምንረዳዉ ማንኛዉም መምህር የንባብ ክሂልን በሚያስተ ምረበት ጊዜ አንብቦ መረዳት በማንበብ ትምህርት ዉስጥ ወሳኝ በመሆኑ በጥሩ ሁኔታ መዘጋጀት እንዳለበት መዘጋጀት እንዳለበት እንረዳለን፡፡ እንደ Pikulski & Chard (2005) አገላለጽ አንብቦ መረዳት ትርጉም ያለዉ ግንዛቤና መልእክት ለማግኘት አንባቢዉ ከሚያነበዉ ጽሁፍ ጋር የሚደርገዉ የሃሳብ ልዉዉጥ የማሰላሰል መስተጋብራዊ ግንኙነት ነዉ፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ የአስተሳሰብ አድማስን ስለሚሰፋ እና በራስ መተማመንን ሰለሚያጎለብት ማንበብሙሉሰዉ ማድረጉን ነዉ ፡፡

ዳዊት (2008) ሰዉ ማወቅ የሚፈልጋቸዉን ነገሮች ሊያገኝ ከሚችልባቸዉ መንገዶች አንዱና ዋነኛዉ ንባብ ነዉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዉች የጠለቀ እዉቀት እንዲኖራቸዉ እና በዚሁ በትምህርታቸዉ የተሻለ ዉጤት እንዲያስመሰግቡ ከሚያስፈልጓቸዉ መሰረታዊ ክህሎች አንዱ የአንብቦ መረዳት ክሂል ነዉ፡፡ በማለት በተጨማሪ ሀሳብ ይገልጻሉ፡፡ ይህ ማለት ምንባብ ለአይምሮ እድገት ወይም ለሚኖረዉ እዉቀት ምንባብ ማንበብና መረዳት ወሳኝ መሆናቸዉን ነዉ፡፡

አንብቦ መረዳት ማለት በጽሁፍ ዉስጥ እንዲተላለፍ የተፈለገዉ መልዕክት በተቻለ መጠን መገንዘብ ነዉ:: አንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳትን ለመመዘን የሚያገለግለዉ ዋና መሳርያ የአንብቦ መረዳት  ችሎታ መለኪያ ፈተና ነዉ፡፡

አንብቦ መረዳት ችሎታ የምንባቡን ጥልቅ መልእክት መረዳትን፣ ከጽሁፍ ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ መረጃዎችን መለየትን፣  ሀሳብን የመገንዘብ ችሎታ ድምር  ሲሆን አጥኚዋ ባዘጋጀችዉ አንብቦ መረዳት ፈተና ተፈትሿል፡፡

### 2.1.7. የአንብቦ መረዳት ችሎታ አይነቶች

Anantasa እና Kemuning (2016) ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ክህሎችን በሚከተለዉ መልክ ገልጸዋቸዋል፡፡

- ✓ የምንባቡን ዋና ሀሳብ መፈለግ

- ✓ በዝርዝር የተገለጹ መረጃዎችን መፈለግ
- ✓ በዝርዝር ያልተገለጹ መረጃዎችን መፈለግ
- ✓ ሊተላለፍ የተፈለገዉን ሀሳብ መረዳት
- ✓ ከቀዳም አንቀጽ ተከታዩን መተንበይ
- ✓ አዉዳዊ ፍች መፈለግ
- ✓ ለቃልት ክፍሎች ትርጉም መስተት
- ✓ ለከባድና ቀላል ቃላት ትርጉም መስጠት
- ✓ ያንቀጽ ሀይለቃል መፈለግ
- ✓ የንባብ ስልቱን መረዳት ነዉ ይላሉ፡፡

### 2.1.8. የአንብቦ መረዳት ችሎታ ደረጃዎች

የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመመዘን የአንብቦ መረዳት ፈተና መስጠት ተገቢ እንደሆነ ከላይ ተገልጿል በመሆኑም ተፈታኙ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አለዉ ወይም የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና ዉጤቱ ከሚጠበቀዉ በታች ነዉ ለማለት እንዲያስችል በፈተና የተገኘዉ ዉጤት ደረጃ ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ Hugete (1989) እንደገለጹት በመርህ ደረጃ ተፈታኞች ለፈተና የቀረበዉን ጽሁፍ ተረድተዉታል ለማለት የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሙሉ በሙሉ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ነገር ግን የሰዉ ልጅ በጽሁፍ የቀረቡ መልእክቶችን ከተለያዩ አቅጣጫ በመመልከት ስለሚገነዘቡ ይህ ብቃት ሁልጊዜ ይኖራል ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም የአንብቦ መረዳት ፈተና ተፈታኞች 80 እና ከ100 በላይ ዉጤት ካስመዘገቡ ጽሁፉን ተረድተዉታል ማለት ያስችላል፡፡

በተጨማሪ ማስተዋል (1989) ሌሎች ምሁራንን ዋቢ በማድረግ እንደጠቀሱት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ደረጃ እንደሚከተለዉ ገልጸዉታል፡፡ በቂ አንብቦ መረዳት ችሎታ አለዉ ሚባል ተማሪ በተለመደዉ ፍጥነቱ በማንበብ በሚሰራዉ አንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና 70% ሊያገኝ ይገባዋል፡፡ ዉጤቱ ከ70% በላይ ከሆነም ጥሩ ችሎታ አለዉ ሊባል ይችላል፡፡ አጥኝዋም ከ 70% በላይ ዉጤት የመጣ ተማሪ ጥሩ ዉጤት እንዳመጣና የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንዳለዉ የማስተዋልን ሀሳብ በመደገፍ ገልጻለች፡፡

### 2.1.9. የአንብቦ መረዳት ክሂል አስፈላጊነት

Ephram (2009) እንደ ገለጸዉ የአንብቦ መረዳት ችሎታ አስፈላጊነት፣ተማሪዎች አዲስ እዉቀት እንዲ ገነቡ እና ሒወታቸዉ የተሳካ እንዲሆን የሚያስችል ነዉ ይላል።

በተመሳሳይ Mothes (1999) ተማሪዎች በማንኛዉም ትምህርት እዉቀት እየገነቡ የመቀጠል ህልዉና በአንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ የተመሰረተ ነዉ። በአንጻሩም ይህ ችሎታ የሌላቸዉ ማንኛዉንም ትምህርት ይቸገራሉ። ከዚህ ከተለያዩ ምንጮች መረጃ የማግኘት ብቃታቸዉ ደካማይሆናል። መምህራን የአንብቦ መረዳት ትምህርትን የማስተማራቸዉ አስፈላጊነት ተማሪዎቻቸዉ በክፍል ዉስጥ የሚማሩትን ትምህርት ለማሳካት ብቻ ሳይሆን በእለት ተእለት የሚያከናዉኗቸዉን ይዘት እንዲያሳኩም ጭምር ነዉ።

Hill አስከትለዉ (2011) የአንብቦ መረዳት መገለጫወች መስተጋብራዊ ሂደትነዉ።በዚህ ሂደት ማለፍ ሲቻል የአንብቦ መረዳቱ ሂደት ያድጋል። በማለት ሲገልጹ የሚነበበዉ ምንባብ ብቻዉን የተሟላ ሳይሆን እንደመነሻ በመሆን ከአንባቢዉ የቀደመ እዉቀት ጋር ማገናኘት አለበት። እንዲሁም የአንብቦ መረዳትን የሚያጎለብቱ ስልቶችን መጠቀምአስፈላጊ እንደሆነ የምሁራኑ ሀሳብ ያስገነዝባል። በጥቅሉ የአንብቦ መረዳት ክሂል ያለፈን መረጃ ከአዲሱ ለማገናኘት በማስቻል ይደፊቱን ለመተንበይ የሚረዳ ወሳኝ ክሂል በመሆኑ ተማሪዎች ይህ ብቃት ካላቸዉ ተፈላጊዉንመረጃ መለየት፣መረዳትና መተረጎም ይችላሉ።ስለዝህ ክሂሉ በቀዳሚ የክፍል ደረጃና ትምህርት ቤቶች ጠንካራ መሰረት ሊኖረዉ ይችላል የሚለዉን ሀሳብ ለማስገንዘብ ነዉ።

እንደገና (1992) የቀደመእዉቀትን መሰረት ያደረገ የንባብ ማስተማርያዘዴ በአማርኛ ቋንቋ እንዲሁም የተለያዩ ምንባቦችን በማንበብ የበለጠ እዉቀት እንዲኖራቸዉ ማንበብ እናም በምንባቡ ዙርያ ሰፊ ማብራርያ መስጠት።

Richardes & Rojers (1986) ምንባብን በምናስተምርበት ጊዜ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ። Gunning (2013) ከላይ በተጠቀሰዉ ሀሳብ በተመሳሳይ ሆኔታ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ በትብብራዊ ንባብን የመማር ሂደት የተማሪዉ ተግባርና ሚና ማማከር መቆጣጠር መመዝገብ እንዲሁም የመረጃ የግብር መልስ ሰጪ ይሆናል ማለት ነዉ።

የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በክፍል ዉስጥ የማስተማር ሂደት ጊዜ በቅድምያ የተማሪዎችን የንባብ ፍላጎት በማነቃቃት ይጀምራል በማለት Williams (1984: 36) ይገልጻሉ፡፡ መምህሩ ምንባቡን ከማስነበቡ በፊት ተማሪዎችን የማነቃቃቱ ቅድመ ምንባብ ተግባራትን ማከናወኑ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት ከመቀስቀሱ ባሻገር ተማሪዎች ስለሚያነቡት ነገር ቅድመ ትንያ እና የኣይምሮ ዝግጅት እንዲያደርጉ ያስችላቸዋል፡፡ ነገርግን መምህሩ ምን ያህል የማነሳሰት እና የማሰተዋወቅ ችሎታ ቢኖረዉም በአንድ ምንባብ የሁሉንም ተማሪዎች ስሜት እና ፍላጎት መገንዘብ አይችሉም፡፡

ከዚህ የምንረዳዉ ስለ ምንባቡ ርእስ ያለንን ቅድመ ንባብ እዉቀት እንዲ ሊሆን ይችላል በማለት መልስ የምሰጥበት ወይም እንዲ ሊሆን ይችላል በማለት ጥያቄ የሚያስከትል የንባብ ሂደት ነዉ፡፡ በዚህ ሰዓት መምህሩ ቅድመ ትንብያዉን እንድንሰጥ አነቃቅቶ ይሆናል ማለት ነዉ፡፡

ተማሪዎች ስለተጻፈዉ ነገር ማስተካከያ የሚሰጡበት እናየተጻፋን ነገር በመረዳት ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች መልስ የምሰጡበት ደረጃ ነዉ፡፡

### 2.1.10. የመምህሩ ሚና

ምንባብን በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ የመምህሩ ሚና ከዘልማዳዊ መምህር ተኮር የተለየ መሆን አለበት፡፡ በዚህም እንደ Johnson et al. (1994) አገላለፅ መምህሩ በእጅጉ የተደራጀ ክፍል ዉስጥ ሁኔታን፣ የንባብ ትምህርት ግብን፣ ለዚም የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሳርያዎችን በማዘጋጀት፣ ምቹ የሆነ አከባቢያዊ የትምህርት አዉድ የመፍጠርና ተገቢ ጊዜ የመስጠት ተግባር ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህም አንጻር የመምህሩ ወሳኝ ሚና የአመቻችነት ሚና ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለተማሪዎች ንባብን የማስተማር ሁኔታ ዉስጥ፣በቡድን አባላት መካከል ያለዉ ትብብራዊ ተግባር ዉስጥ መምህሩ ማንኛዉንም እርዳታ ፈላጊ ጥያቄ ሲኖር የመርዳትና አቅጣቻ የማሳየት ሚና ይኖረዋል፡፡ለተማሪዎች ግልጽ እና አጠር ያለ ትምህርት በማስተማር ተማሪዎች እንዲሳተፉ ማድረግ፡፡ እንዲሁምለምንባብ ትምህርቱ የሚያገለግል የትምህረት መርጃ መሳርያ ማዘጋጀት፡፡

- የተንዛዛ ትምህርት አለማስተር ማለተም አሰልቺ የሆነ ትምህርት እነዲሁም የንባብ ችሎታቸዉ እንዲሰፋ ከተለያዩ መፀሀፎች ምንባብ በማዉጣት ጥያቄ በመስጠት በጥያቄዎች መልስ እነዲሰጡ ማበረታታት፡፡

### 2.1.11. የተማሪዉ ሚና

የእለቱን ትምህርት በጥሞና በመከታተል ምንባቡን በራስ ተነሳሽነት ማንበብ የተሰጡትን የቅድመ ምንባብና ድህረ ምንባብ ጥያቄዎችን በመስራት ለመምህሩ ማሳየት፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን መምህሩ አንድን ምንባብ በሚያስተምርበት ጊዜ በዚያ ርእስ ዙርያ በመወያየት ለችግሩ መፍትሄ መስጠት እና ተመራማሪ መሆን፡፡

## 2.2. የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ክፍል ዉስጥ ከዚህ ጥናት ጋር የሚዛመዱ ጥናቶች ይዳሰሳሉ፡፡ በጥናቱ ስራዎች ዉስጥ የሚወሰዱ ሀሳቦች የጥናቱ ርእስ፤ የጥናቱ ዓላማ የጥናቱ ዘዴእና የመፍትሄ ሀሳቦች ይጠቀሳሉ፡፡ ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ባይኖርም ተመሳሳይነት /ተቀራራቢነት/ካሉት ጥናቶች መካከል ፋሲካ ዉበቱና አገኘሁ ተስፋ (2018) በትብብር መማር በአንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት ለይ ያለዉ ሚና በሚል ርእስ በጎንደር ከተማ ፋሲለደስ መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጥናት አካሂደዋል ጥናቱም በሙራከራ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የተጠኝዎች ምርጫ በእድል ሰጭ ናሙናየተመረጠነዉ፡፡ እንዲሁም የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዉ ፈተናና የጽሁፍ መጠይቅ ሲሆኑ ከድህረና ቅድመ ትምህት ተሰብስቦ የተገኘዉን የፈተና ዉጤት በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተሰልቶ በspss መረጃ መተንተኛ ሶፍት ዌር ተግባራዊ አድርገዉታል፡፡ጥናቱም ፍጥነታዊ የምርምር ስልትን ተከትሎ የተከናወነ ነዉ፡፡ በጥናታቸዉ መጨረሻ ላይ ያገኙት ዉጤትም በትብብር መማር የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ማሻሻሉን ካገኙት ዉጤት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ይሄንን ጥናት ከአጥኝዋ ጥናት ጋር የሚያመሳስለዉ አንደኛ ተማሪዎች እርስ በርሳቸዉ በመተባበር የሚማሩት ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉ አስተዋፆ አለዉ? የሚለዉ እና የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ ፈተና መሆኑ እንዲሁም ከፈተና የተገኘዉ ዉጤት በቲ-ስቴት ቀመር ተሰልቶ በspss መተንተኑ የሚያመሳስለዉ ሲሆን የሚያለያየዉ ደግሞ እነሱ በአማራ ክልል ፋሲለደስ መሰናዶ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል ላይ መሰራቱ እና አጥኝዋ በ9ኛ ክፍልን መምረጧ ነዉ፡፡

የማርያም ወረቅ (2013) በኢትዮ ምሊኒዬም 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 6ኛ ክፍል ተማሪዎች የመደገፍ ብለሀቶች የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማዳበር ያለዉ ሚና በሚል ርእስ የተካሄደ ጥናትሲሆ፡፡ የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ተማሪዎች ከምንባቡ ለወጡ ጥያቄዎች ዝቅተኛ የአፈጻጸም ደረጃ ማሳየታቸዉን በመገንዘቧ ነዉ፡፡

ጥናቱ የተካሄደበት ዘዴ መጠናዊ ሲሆን የተከተለዉ የምርምር ስልትም ባለሁለት ቡድን ምስል ፍጥነታዊ ሲሆን የጥናቱ ተሳታፊዎች እትዮ-ምሊኒዬም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ የሚማሩ የ6ኛ ክፍል ተማሪዎች በተራ የእጣ ናሙና አመራረጥ የተመረጡ ናቸዉ ከተጠኝዎች በፈተናና በፅሁፍ መጠይቅ የተገነዉን መረጃ በባእድ ናሙና ቲ-ቴስት እና በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ በዚህ ጥናት ዉስጥም በሁለቱ ቡድኖች በቅድመ ትምህርት

ፈተና መካከል ልዩነት አለመኖሩን ነገር ግን በሁለቱ ቡድኖ ድህረ ፈተና ላይ ጉልህ የአንብቦ መረዳት ችሎታና የአንብቦ መረዳት ተነሳሽነት መኖሩን በጥናቷ ላይ አረጋግጣለች። በዚህጥናት ዉስጥም በመደገፍ ብለሀቶች በተማሪዎች አብብቦ መረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ላይ በወንድና በሴት ተማሪዎች መካከል ልዩነት የለም የሚል እድምታ አግኝታለች።

አንድነት (2010) በበቶ ሙሉ አንደኛ ደረጃት ምህርት ቤት ላይ ከላይ-ታችና ከታች-ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት ክሂል ያላቸዉን አስተዋጽኦ በማነፃጸር የተሻለዉን ሞዴል ለመለየት 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ ጥናት ነው። ይህ ጥናት የተካሄደዉ በጋሞጎፋ ዞን በኡባ ደብረ ፀሐይ ወረዳ ነዉ። ይህ ት/ቤት ካሉት ት/ቤቶች በአመቺ ናሙና የአመራረጥ ዘዴ የተመረጠ ሲሆን የመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዉ ፈተኛ፣ ምልከታ፣ የፅሁፍ መጠይቅ ናቸዉ በዚህ ጥናት ዉስጥ የተሳተፉት የተጠኝዎች ብዛት 45 እና ከዚያ በላይ ናቸዉ።

በዚህ ጥናት ዉስጥም በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ችሎታቸዉን ከፍ ለማድረግ የሚረዳ ሞዴል የላይ ታች የማናበብ ክሂል ማስተማርያ ሞዴል መሆኑን በጥናቱ አረጋጧል። በመጨረሻም የመፍትሄ ሃሳብ ብሎ ካስቀመጣቸዉ አንዱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የማንበብ ትምህርቱን ተማሪዎች በግላቸዉ እያነበቡ የሚማሩበት ሁኔታ ቢመቻች የሚልነዉ። የመረጃ መተንተኛ ዘዴዉም በቲ ቴስት ተሰልቶ ከቲ ሰንጠረዥ ዋጋ ጋር በማነፃፀር የተገኘዉን ዉጤት መተንተን ነዉ። ይሄንን ጥናት ከዚህ ጥናትጋር የሚያመሳስለዉ ከአራቱ ክህሎች በተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታላይ ማተኮሩ ከመረጃ መሰብሰብያ መሳርያዎች በፈተና በምልከታ መጠቀሙ። እንዲሁም ልይይት ፣መደበኛ ልይይት፣ አማካይ ዉጠየትን በመጠቀም መረጃን መተንተኑ እና ሙከራዊ የምርምር አይነትን መጠቀሙነው።

የሚያለያየዉ ደግሞ ይህ ጥናት ተማሪ-ተኮር የመማር ማስተማር ሂደትን ሲጠቀም የሱደግሞ በላይ-ታችና በታች-ላይ ሞዴል መጠቀሙ፣ እሱ በጋሞ ጎፋ ዞን በኡባ ደብረ ፀሀይ ወረዳ ጥናቱን ሲያካሂድ ይህ ጥናት ደግሞ በኢሉባቦር ዞን በብርብርሳ ወረዳ መካሄዱ፣ ይህ ጥናት የ9ኛ ክፍል ተማሪዎቸን ተተኳሪ ሲያደርግ የሱ ደግሞ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ማድረጉ ነው።

እቴነሽ (2010) በአማርና ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የማንበብ ልምድና አንብቦ መረዳት ችሎታ ተዛምዶ በዳባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት

በሚል ርእስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ ባካሄደችዉ ጥናት የተጠቀመቸዉ የጥናት አይነት መጠናዊ ሆኖ ተዛምዶአዊ ምርምር ስልትን የተከተለ ነዉ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴም የፅሁፍ መጠይቅ እና ፈተና ናቸዉ፡፡ የጥናቱ ተጠኝዎች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ሲሆኑ አመራረጡም የእጣ ናሙና አመራረጥ ን በመጠቀም ነዉ፡፡ የተሰበሰበዉ መረጃ የፐርሰንት የተዛምዶ መለክያ ወሳኝ ቀመር የተተነተነ ሲሆን በተጨማሪም በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለዉ የማንበብ ልምድን አንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ደግሞ በነፃ ናሙና ቲ-ቴስት ቀመር ተንትናለች፡፡

በመጨረሻም የሰጠችዉ የመፍትሔ ሀሳብም በርእሱ ዙርያ ተጨማሪ ጥናት የሚያደርጉ ተመራማሪዎች ይሄንን ጥናት እንደ መነሻ በማድረግ ከዚህ የተሸለ ጥናት ለማካሄድ ጥረት ቢያደረጉ የሚል ነዉ፡፡ ይሄንን ጥናት ከእቴነሸ ጥናት ጋር ያመሳሰለዉ በ9ኛ ክፍል በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ መሰራቱ፣ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዋ ፈተና መሆኑ፣ እንዲሁም ከፈተና የተገኘዉን ዉጤት በቲ-ቴስት ቀመር መተንተኗ ነዉ፡፡ የሚያለያየዉ ደግሞ የጥናቱ አይነት መጠናዊ ሆኖ ተዛምዷዊ መሆኑ፣ በዳባት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ መሰራቱ፣ የአንብቦ መረዳት ችሎታ የንባብ ልምድ መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመፈተሽ ሁለት መተንተኛ ዘዴዎችን መጠቀሟ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

ከዚህ ዋና ጥናት የምርምር ስልት የጥናቱ ተሳታፊዎች አመራረጥ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣርያዎች የአጠናን ሂደት የማስተማሪያ ትግበራ የመረጃ አተናተን ስለሰቶች ይብራራሉ።

### 3.1. የጥናቱ ንድፍ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ አስተዋጽኦ ማድረግ አለማድረጉን መመርመር ነዉ።

አጥኚዋ ይሄንን ጥናት ለማካሄድ የተጠቀመችዉ ሙከራዊ የምርምር አይነት ሲሆን መጠናዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ነዉ። ከችሎታ መለኪያ በፈተና በጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለተገኘዉ ምላሽ መለየ (ኮድ) በመስጠት በሰንጠረዥ በማቅረብ በገላጭ እስታትስቲክስ ተተንትኖ ቀርቧል።

### 3.2. **የጥናቱ አካላይ**

ይህ ጥናት የተካሄደዉ በኢሉ አባቦራ ዞን ሰሌ ኖኖ ወረዳ ብረብረሳ ቀበሌ ዉስጥ ነዉ ። በዘህም ወረዳ ዉስጥ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ሁለት ሲሆኑ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ዉስጥ የሚገኑ ተማሪዎች ብዛት በኮምቦልቻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሴት 185 ወንድ 235 በአጠቃላ በዚህ ትምህርትቤት ዉስጥ 420 ተማሪዎች የሚገኙ ስሆን በቢርቢርሳ ሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሴት ተማሪዎች 300 ወንድ 310 በአጠቃላይ 610 ተማሪዎች ይገኛሉ።

ለዚህ ጥናት የተመረጠዉ ትምህርትቤት የብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2013 ዓ.ም በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ናቸዉ። ለዚህጥናት የተመረጡት 9ኛ ክፍል የሚማሩ ከ240 ተማሪዎች 80ተማሪዎች ናቸዉ።

### 3.2.1 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

### 3.2.2 የትምህርት ቤት ምርጫ

ለጥናቱ የተመረጠዉ ትምህርት ቤት በኢሉባቦር ዞን በኖኖ ሰሌ ወረዳ የብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነዉ። የተመረጠዉ በአመቺ ናሙና ስልት ነዉ። ትምህርት ቤቱ የተመረጠበት ምክንያቱም አጥኝዋ በመምህርነት ለ8 አመት የሰራችበት በመሆኑና አሁንም እዚያዉ ትምህርት ቤት እየሰራች ስለሆነ የአከባቢዉን ሁኔታ በደንብ ስለምታዉቀዉና ጥናቱን በምታካሂድበት ጊዜ መረጃዉን በተገቢዉ መንገድ መሰብሰብ ስለሚያስችል ነዉ።

### 3.2.3. የመማሪያ ክፍል ምርጫ

ለጥናቱ የተመረጠዉ የክፍል ደረጃ ዘጠነኛ (9ኛ) ክፍል ነዉ፡፡ የክፍል ደረጃ የተመረጠበት የንሞና ዘዴ አመቺ የንሞና ዘዴ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ይህ የክፍል ደረጃ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደትን በምታስተምርበት ጊዜ የማስተማር ሂደቱ ለተማሪዉ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉን አስተዋጽኦ ለመረዳት አጥኝዋና ተጠኝዎችን አንድ ላይ የሚያገናኝ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.2.4 የተጠኚዎች ምርጫ

አጥኚዋ ትኩረት አድርጋ ለማጥናት ያቀደችዉ የ9ኛ ክፍል ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዉ የአንብቦ መረዳት ቸሎታ የለዉን አስተዋጽኦ ለመረዳት ነዉ፡፡ ከ9A-F ካሉት 240 ተማሪዎች 9ኛA እና B 80 ተማሪዎችን እድል ሰጪ ናሙናን በመጠቀም ከመረጠች በኋላ ፈተናን እና የፅሁፍ መጠይቅ በማከናወን ጥናቱን አካሂዳለች፡፡

### 3.2.5. የመምህር አመራረጥ

የመምህር ምርጫን በተመለከተ በኢሉ አባቦር ሰሌ ኖኖ በብርብርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ ሁለት የአማርኛ መምህራን ብቻ የሚገኙ ሲሆን እነሱን በጠቅላይ ናሙና ተወስዷል፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ

የምርምር መረጃ ተአማኒነት፤ አስተማማኝ እና ትክክለኛነት ከሚወስኑ በጣም አስፈላጊ ነገሮች የመረጃ መሰብሰብያዎቹ ጥንካሬ የመረጃዉን ደረጃ ይይዛል፡፡ በምርምሩ ሂደት እንደ ምርምሩ አይነት፣ እንደ ተጠኚዎቹ ሁኔታ፣ እንደ ተመራማሪዉ ችሎታ፣ ምርምሩን ለማካሄድ እንዳለዉ የገንዘብ እና የጊዜ መጠን፣ የስልትና ፍልስፍና ሁኔታ፣ ለመረጃ መሰብሰብያነት የሚያገለግሉ በርካታ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች አሉ፡፡ እነዚህም ዘዴዎች በመጀመሪያ በይዘቱ ዙሪያ ተማሪዎች ምን ያህል እንደ ተገነዘቡ ለማረጋገጥ ፈተና በመፈተን የተማሪዉ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለመረዳትም የፅሁፍ መጠይቅ ተካሂዷል፡፡ ከተካሄደዉ የፅሁፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎችም በቅደም ተከተል ተከናዉነዋል፡፡ እነሱም ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ ናቸዉ፡፡

3.3.1. **አንብቦ መረዳት ፈተና**

ፈተና የተለያዩ አለማዎችን መሰረት በማድረግ የሚሰጥ ነዉ፡፡ የሚሰጥበት አላማ መለያየት ለፈተና አይነቶች መለያየት ምክንያት እንደሆኑ የመስኩ ምሁራን ይገልጻሉ፡፡ ለምሳሌ Harrison (1983) ፈተናን በአይነት በአይነት ለመመደብ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮችን አስመልክቶ ሲገልጹ ፈተና የምንፈትን በትን አላማ ማወቅ የፈተናዉን አይነት እንድንለይ ያስችለናል በማለት ያስረዳሉ

ያለዉ (2009፡19) በበኩላቸዉ የፈተናዎችን ይዘትና አይነት የሚወስነዉ ዋና ነገር ፈተናዎቹ የተዘጋጁበት አላማ ነዉ፡፡ በማለት ከHarrison (1983) ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ይገልጻሉ፡፡

ፈተናዎች በተለያዩ መልኮች ተዘጋጅተዉና በጥንቃቄ ተቀናጅተዉ አስፈላጊዉን መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላሉ፡፡ እንደ Rant Nuke (2012) አገላለጽ ይህ ፈተና የተማሪዎችን ብቃት ለመፈተሽ የሚያገለግል ነዉ ይላሉ፡፡ በተለይ ተጨባጭ የሆነ እዉቀትና ችሎታን ይለካል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን Annie (2011) የብቃት መለክያ ፈተና አንድን ነገር የመያዝ፣ የመገንዘብ፣ ጥልቅ የቋንቋ ክሂል ችሎታ እንዲኖረን ያደርጋል ይላል፡፡

ለዚህ ጥናትም ያገለገለዉ የፈተና አይነት የችሎታ መለኪ ፈተና ነዉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያትም የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ማለትም በሚያነቡበት ጊዜ ምን ተገነዘቡ ምን ችሎታ አገኙ የሚለዉን ስለሚጠይቅ ነዉ፡፡

የተወሰኑ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዉ ወጥነት ባለዉ መንገድ የተፈታኞችን አእምሯዊ ወይም ስነ ባህሪያዊ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃን ለመሰብሰብ የሚረዳ መለኪያ ነዉ፡፡ ወጥነት ሲባል ፈተነዉ ለጥናቱ ተሳታፊዎች የሚሰጠዉ በተመሳሳይ ሁኔታ ማለትም በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ የአፈታተንና የአስተራረም መንገድ ተመሳሳይ የመልስ አሰጣጥ መልክና መመሪያ ከተቻለ በተመሳሳይ ፈታኝ የሚካሄድ መሆኑን ለማመልከት ነዉ፡፡

ይህ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ አጥኚዋ ፈተናዉን ከረዳት መምህሯ ጋር በመሆን በመፈተን መረጃዉን ስለምታገኝ  ይሄንን የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ በመምረጥ ትጠቀማለች፡፡ በዚህ የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴ ዉስጥ ቅድመ ትምህርት ፈተናና ድህረትምህርት ፈተና የሚያካትት ይሆናል፡፡ የዚህ ጥናት ፈተናም ሁለት አለማዎች ያሉት ሲሆን ይህም የተጠኝ ተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና በአጥኝዋ  የተዘጋጁ ሲሆን የመጀመሪያዉ ቅድመ-ትምህርት

ፈተና አላማዉ የሚሰጥበት ኣላማ ተማሪዎች ከጥናቱ በፊት ያላቸዉን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ተመጣጣኝ መሆን አለመሆኑን ለመፈተሽ ነዉ፡፡ የሁለተኛዉ ድህረ-ትምህርት አላማም የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በተለያዩ የማስተማር ብልሀቶች ከተማሩ በኋላ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸዉ መሻሻል አለመሻሻሉን ለማረጋገጥ እና ስለ ምንባቡ ማወቅ አለማወቃቸዉን ለመለየት ነዉ፡፡ ቅድመና ድህረ ፈተናዎች ከሁለቱ ቡድን ተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልትን የተከተሉ ሆነዉ የተለያዩ ጥያቄዎች ወጥተዉ ተፈትነዋል፡፡

የንባብ ተግባራቱም ሁለት የተለያዩ ርእሰ ከ9ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ዉስጥ በመምረጥ ወንድም አማቾች የሚል ርዕስ ከምእራፍ አራት ገጽ 54-59ና ሁለተኛዉ ደግሞ ክርክር/ሙግት ምንባብ ከምእራፍ አስር 165-169 ከተዘጋጁ በኋላ ለተተኳሪ ተማሪዎች ፈተናዉ ቀርቦ ተፈትነዋል:: የተዘጋጀዉ የፈተና ይዘትን በሚመለከትም 7 ክፍሎች ያሉት ጥያቄ ያካተተ ሲሆን እዉነት/ሀሰት 10 አዛምድ፣ 10 ምርጫ፣ 10 ለቃል ፍቺ መስጠት፣ 5 አብራራ፣ 5 ባዶ ቦታ ሙላ፣ 5 አጭር መልስ ስጥ እና 5 በማዘጋጀት በቅድመና ድህረ-ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመለየት ፈተናዉ ተሰጥቷል፡፡ ለጥያቄዎች የተሰጠዉ ነጥብ (50%) የያንዳንዳቸዉ ጥያቄዎች የይዘት ነጥብም እንደ ጥያቄዎች ባህሪያት ክብደትና ቅሌታቸዉን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ነበሩ፡፡ እርማቱን በተመለከተ የተጠኝዎችን አቅም ከግምት ዉስጥ በማስገባት እዉነት/ሀሰት፣ ምርጫ፣ አዛምድ የቃል መጥበቅና መላላት ፍቺ፣ ባዶ ቦታ ሙላና አጭር መልስ ስጥ ተካቶ በተመረጠችዉ መምህር ታርሟል፡፡

ከአንብቦ መረዳት ፈተናዎች ከሙከራ ጥናት በፊት የይዘት ትክክለኛነታቸዉን በተለየ መልኩ ለመገምገም ተችሏል፡፡ የፈተናዉን ትክክለኛነት ለመጠበቅ ሲባል የ9ኛ ክፍልን መማሪያ መጽሀፍ፣ ትምህርት መሰረት በማድረግ ተዘጋጅቶ ተፈትነዋል፡፡

### 3.3.2. የፅሁፍ መጠይቅ

የፅሁፍ መጠይቅ ከሌሎች የመረጃ መሰብሰብያ ዘዴዎች ጋር ሲነጻጸር ጊዜን፣ጉልበትን እና ገንዘብን ይቆጥባል፡፡ ይህም ሲባል ተመራማሪዉ መጠይቁን ካዘጋጀ በኋላ መረጃዉን ለመሰብሰብ ከእያንዳንዱ ተጠኝ ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት በእያንዳንዱ ጥያቄ ላይ አይወያይም፣ማብራርያ በመስጠትም ጊዜ አያጠፋም አንዳንድ ጊዜ ጋር ፊት ለፊት ከሰዎች ጋር በመነጋገር ስለሚጠየቁት ጉዳይ መልስ ለመስጠት የማይደፍሩ/የማይፈልጉ መላሾች

በፅሁፍ መጠይቅ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት ይችላሉ፤ ይሄንን መሰረት በማድረግ የጽሁፍ መጠይቁ በዚህ ጥናት ዉስጥ ሁለተኛ መረጃ መሰብሰብያ ሆኖ አገልግሏል፡፡

### 3.4 የማስተማሪያ መሳርያ ዝግጅትና የማስተማር ትግበራ

#### 3.4.1 የማስተማሪያ መሳሪያ ዝግጅት

የትምህርት መስተማሪያ መሳሪያዎች ተማሪዎች ለሚከናዉኑት ለንባብ ትምህረት ከፍተኛ ሚና አለዉ፡፡ተመሳሳይ የትምህርት መሳርያዎችን በተለያዩ የትምህርት አዉድና ሁኔታዎች ዉስጥ ተግባራቸዉን ለይተን ልንጠቀምባቸዉ እንችላለን (Johnson et al. 1994).

ይህ ማለት ለምሳሌ አንድን አጭር ለልቦለድ ለማንበብ ከመረጥን በኋላ ምንባቡን በመሃል እያቆምን የምንባቡን የምንባብ ጊዜ ክንዉን እንዲናገሩ በማድረግ ንግግር እናዳብርበታለን፣ እንዲሁም የልቦለዱን መልእክት በጽሁፍ እንዲጽፉ በማድረግ ጽህፈትን እናስተምራለን ከዚህ አንጻር አንድን የትምህርት መረጃ መሳርያ በተለያዩ የትምህርት አዉድ ውስጥ ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡

በዚህ ጥናት የአንብቦ መረዳት ትምህርት ትግበራ ላይ መምህሯ ትኩረት ያደረገችዉ የተማሪዉን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ሲሆን የተጠቀመችዉም የ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማርያ መፅሀፍ ብቻ ነዉ፡፡ከማስተማርያ መሳርያ አጠቃቀም አንጻር ዝቅተኛ መሆኑን እንረዳልን፡፡

#### 3.4.2 የማስተማር ትግበራ

የዚህ ጥናት የመማር ማስተማር ትግበራ ለሁለት ሳምንታት ተካሂዷል ይሄንን ትግበራ ለማከነወን በአላማዊ የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተተኳሪዎቹን ለማስተማር አንድ ሴት መምህር በመምረጥ ለተመረጠችዉ መምህርት ስለተማሪተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለአንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉን አስተዋጾ ለአራት ቀን ያህል ሀሳብ በመለዋወጥ ወይም በመወያየት በመማር ማስተማሩ ሂደት ተተኳሪ የሆኑ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖች ተመሳሳይ ይዘትን ቅድመ እና ድህረ ትምህርት በአንድ መምህር ተምረዉ ፈተና የተፈተኑ ሲሆን ሁለቱም ቡድኖች ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደትን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ችሎታዉ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ተማሪዎችን ከመደበኛ ትምህርታቸዉ ዉጪ ባለዉ ትርፍ ሰዓት እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ በሙከራ እና በቁጥጥር ቡድን ዉስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ትምህርታቸዉን ሲማሩ ከጊዜ አኳያ ያለዉን ለዉጥ ለመቆጣጠር አንዱ ቡድን በመጀመርያ

ክፍለ ጊዜ ከተማሩ በሌለኛው ሳምንት ሁለተኛዉን ክፍለ ጊዜ እንዲማሩ የማድረግ ስራ ተከናዉኗል፡፡

ይሄንንም ለማረጋገጥ የሙከራ ቡድን የንባብ ጊዜ ትግበራ እና ቁጥጥር ቡድብ የንባብ ጊዜ ትግበራን ለማየት ተችሏል፡፡

ይህ ሲከናወን በቅደመ ትምህርቱ ላይ ሁለቱንም ቡድን በአንድ የመማር ማስተማር ዘዴ ከተማሩ በኃላ በሁለተኛዉ ሳምንት ግን ሁለቱንም ቡድን የተለያየ ማለትም ተማሪ ተኮር እና በተለምዶ መምህር መራሽ እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ ይህ ሲሆን  የሙከራ ቡድንን በተማሪ ተኮረ፣ የቁጥጥር ቡድንን በተለምዶ እንዲማሩ ከተደረገ በኃላ ትኩረት የተደረገበት የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዉ አንብቦ መረዳት ያለዉን አስተዋፅኦ ለመለየት ፈተና በተመሳሳይ ሰዓት እና በተመሳሳይ የአጠያየቅ ስልት ተፈትነዋል፡

### 3.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

አጥኚዋ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ምን አይነት አስተዋጽኦ አለዉ የሚለዉን ጥያቄ ጥናቱ ዉስጥ ለመመለስ/ጥናቱን ከግብ ለማድረስ በዋናነት ፈተና በመፈተን እና የጽሁፍ መጠይቅ አዘጋጅቶ በመጠየቅ ነዉ፡፡ይህ የሆነበት ምክንያትም የተማሪዉን አንብቦ መረዳት እና የአነባብ ደረጃ ለመለየት ስለሚጠቅም ነዉ፡፡ መረጃዎችን ከሰበሰበች በኋላ የተገኙትን መረጃዎች ትክክለኛነት በማየት የተሰበሰበዉን መረጃ /ምላሽ/ ከጣራች በኋላ ለመልሱ መለያ (ኮድ) ሰጥታለች በመቀጠል መረጃ መመዝገብያ ሰንጠረዥ በማዘጋጀት ከእያንዳንዱ የተገኘዉን መረጃ ሙከራዊ የምርምር ስልትን በመጠቀም ከተማሪ በፈተና የተገኘዉን መረጃ ስታቲስቲክሳዊ መረጃ መሰረት በማድረግ በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ልይይት፣ መደበኛ ልይይት እና አማካይ ዉጤት ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.የመረጃ ትንተና እና ማብራሪያ

### 4.1 የመረጃ ትንተና

#### 4.1.1 ከፈተና የተገኘ መረጃ ትንተና

ከዚህ በታች የሚታየዉ ሰንጠረዥ የተማሪዉን የቅድመ ትምህርት ፈተና ና የድህረትምህርት ፈተና ዉጤትን የሚያሳይ ሲሆን ለፈተናዉ አስተማማኝነትም አስፈላጊ ስለሆነ የእያንዳንዱ ተማሪ ዉጤት በዚህ መልኩ ተቀምጧል። ፈተናዉም የሙከራና የቁጥጥር ቡድን ዉጤት ነዉ።

ሰንጠረዥ 1. የሁለቱን ቡድን የቅድመ ፈተና ዉጤት የሚያሳይ

| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት | | | | የቁጥጥር ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት | ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት | ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት | ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት |
| 1 | 30 | 21 | 29 | 1 | 28 | 21 | 20 |
| 2 | 29 | 22 | 30 | 2 | 30 | 22 | 21 |
| 3 | 30 | 23 | 31 | 3 | 28 | 23 | 22 |
| 4 | 30 | 24 | 32 | 4 | 25 | 24 | 24 |
| 5 | 28 | 25 | 32 | 5 | 27 | 25 | 25 |
| 6 | 32 | 26 | 30 | 6 | 26 | 26 | 24 |
| 7 | 33 | 27 | 33 | 7 | 22 | 27 | 22 |
| 8 | 33 | 28 | 27 | 8 | 24 | 28 | 24 |
| 9 | 34 | 29 | 26 | 9 | 22 | 29 | 23 |
| 10 | 33 | 30 | 26 | 10 | 23 | 30 | 24 |
| 11 | 30 | 31 | 28 | 11 | 25 | 31 | 26 |
| 12 | 29 | 32 | 25 | 12 | 23 | 32 | 24 |
| 13 | 28 | 33 | 24 | 13 | 28 | 33 | 28 |
| 14 | 28 | 34 | 21 | 14 | 26 | 34 | 21 |
| 15 | 30 | 35 | 23 | 15 | 25 | 35 | 23 |
| 16 | 29 | 36 | 24 | 16 | 26 | 36 | 20 |
| 17 | 30 | 37 | 30 | 17 | 25 | 37 | 19 |
| 18 | 28 | 38 | 29 | 18 | 29 | 38 | 20 |
| 19 | 27 | 39 | 28 | 19 | 28 | 39 | 28 |
| 20 | 27 | 40 | 28 | 20 | 30 | 40 | 20 |

## ሰንጠረዥ 2. የሁለቱ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና

| ፈተና | የቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | የቲ. ተስት ዋጋ | 95% የስህተት ይሁንታ መጠን | | የነፃነት ደረጃ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | X | x̄ | S | Sd | | ከፍተኛ | ዝቅተኛ | | |
| የሙከራ ቡድን | 40 | 1154 | 28.85 | 8.490 | 2.9137 | 62.622 | 34.0 | 21.0 | 39 | 000 |
| የቁጥጥር ቡድን | 40 | 970 | 24.25 | 8.910 | 2.9974 | 51.38 | 30 | 19 | 39 | 000 |

ሰንጠረዥ እንደ የሚያመለክተዉ የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት አማካይ ዉጤት=28.85 መደበኛ ልይይት=2.9137 ከቁጥጥር ቡድን አማካይ=24.25 መደበኛ ልይይት =2.9974) ጋር ሲነፃፀር የተገኘዉ ዉጤት ተቀራራቢነት አለዉ፤ ማለትም ልዩነት የለዉም፡፡ የሁለቱ ቡድን መደበኛ ልይይት ተቀራራቢ መሆን የጥናቱ ተሳታፊዎች አማካይ ዉጤት ያለዉ ርቀት ተቀራራቢ መሆኑን ያሳያል፡፡ይሁን እንጂ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለዉን የዉጤት ተመጣጣኝነት ትክክለኛመሆን አለመሆኑን ለማረጋገጥ ዳግም ጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡ ጥንድ ናሙና ቲ-ቴሰት ማለትሁለት ዝምድና የሌላቸዉን ነፃ የሆኑ ቡድኖችን በመዉሰድ በአንድ በተመረጠ ተለዋዋጭ ወይም ባህሪ አንፃር ልዩነት እነዳላቸዉና እንደሌላቸዉ ለመወሰን የምንጠቀምበት ስልት ነዉ፡፡

በመሆኑም  በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና ከልይይት ከአማከይ ዉጤት አንር የጎላ ልዩነት አለመኖሩን የተገኘዉ ዉጤት ያስረዳል፡፡ይህ ማለት ሁለቱ ቡድኖች ተቀራራቢ የሆነ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እነዳላቸዉ ያሳያል የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት ተማሪወች ከተለማመዱ በኋላ ተፈትነዉ ያመጡት የአንብቦ መረዳት ችሎታ ዉጤት እንደሚከተለዉ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## ሰንጠረዥ 3. የድህረ-ፈተና ትምህርት ዉጤት

| የሙከራ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት | | | | የቁጥጥር ቡድን  ቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት | ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት | ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት | ተ.ቁ | የተማሪዉ ዉጤት |
| 1 | 38 | 21 | 29 | 1 | 30 | 21 | 32 |
| 2 | 36 | 22 | 28 | 2 | 29 | 22 | 34 |
| 3 | 30 | 23 | 35 | 3 | 33 | 23 | 28 |
| 4 | 34 | 24 | 34 | 4 | 32 | 24 | 28 |
| 5 | 33 | 25 | 33 | 5 | 30 | 25 | 30 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | 30 | 26 | 34 | 6 | 29 | 26 | 35 |
| 7 | 33 | 27 | 33 | 7 | 33 | 27 | 36 |
| 8 | 34 | 28 | 32 | 8 | 22 | 28 | 32 |
| 9 | 34 | 29 | 33 | 9 | 34 | 29 | 33 |
| 10 | 32 | 30 | 35 | 10 | 23 | 30 | 34 |
| 11 | 35 | 31 | 29 | 11 | 32 | 31 | 26 |
| 12 | 36 | 32 | 30 | 12 | 30 | 32 | 29 |
| 13 | 36 | 33 | 33 | 13 | 29 | 33 | 30 |
| 14 | 37 | 34 | 30 | 14 | 33 | 34 | 33 |
| 15 | 30 | 35 | 40 | 15 | 35 | 35 | 35 |
| 16 | 39 | 36 | 35 | 16 | 34 | 36 | 34 |
| 17 | 33 | 37 | 40 | 17 | 36 | 37 | 33 |
| 18 | 33 | 38 | 32 | 18 | 34 | 38 | 30 |
| 19 | 32 | 39 | 33 | 19 | 30 | 39 | 29 |
| 20 | 29 | 40 | 30 | 20 | 30 | 40 | 33 |

**ሰንጠረዥ 4. የድህረ ልምምድ ፈተና ጠቅለል ባለ መልኩ የሚያሳይ**

| ፈተና | የቅድመ ትምህርት ፈተና | | | | | የቲ. ተስት ዋጋ | 95% የስህተት ይሁንታ መጠን | | የነፃነት ደረጃ | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | X | x̄ | S | sd | | ከፍተኛ | ዝቅተኛ | | |
| **የሙከራ ቡድን** | 40 | 1332 | 33.3 | 10.162 | 3.1881 | 70.263 | 40 | 28 | 39 | 197 |
| **የቁጥጥር ቡድን** | 40 | 1252 | 31.3 | 8.985 | 2.9974 | 62.093 | 36 | 22 | 39 | 119 |

ሰንጠረዥ 2 የሙከራ እና የቁጥጥር ቡድን ድህረ-ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና ዉጤት ያሳያል፡፡ ሰንጠረዡ እንደሚያስረዳዉ የሙከራ ቡድን አንብቦ መረዳት ድህረ-ትምህርት ፈተና አማካይ ዉጤት=33.3 መደበኛ ልይይት 3.1881 ከቁጥትር ቡድን አማካይ ዉጤት=31.3 መደበኛ ልይይት=2.9974 የሙከራ ቡድን አንብቦ መረዳት አማካይ ዉጤት ከቁጥጥረ ቡደን በ.2 በልጦ ይገኛል፡፡ ይህ ማለት ከቁጥጥር ቡድን ድህረትምህርት ፍተና የሙከራቡድን ድህረ ትምህርት ፈተና ጉልህ ልዩነት እንዳለዉ ያሳያል፡፡ ልዩነቱ የተገኘዉም እያንዳንዱ የተማሪ ዉጤት በመደመር ለተማሪ ብዛት በማካፈል እና የተገኘዉን ዉጤት በspss ፎረሙላን በመጠቀም ነዉ፡፡ ለዚህ ምርምር መላምት ሆኖ ያገለገለዉ ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ባለ ሁለት ጫፍ ነዉ፡፡ በአጠቃላይ በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ታግዘዉ የአንብቦ መረዳት ትምህርትን በተማሩ የሙከራ ቡድን በተለምዶ የማስተማር ዘዶ በተማሩ

የቁጥጥር ቡድን ተሳታፊዎች መካከል  ጉልህ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ልዩነት እንዳለዉ ያሳያል፡፡

ስለዚህ በዚህ ጥናት ዉስጥ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ከተለምዷዊዉ የአንብቦ ማስተማር ዘዴ በበለጠ ሁኔታ የተማሪዎችን  የአንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያዳብር መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህ ስታትስቲካዊ ስሌት ተማሪ ተኮር ማስተማር ዘዴ  በተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ላይ ለዉጥ እንዲመጣ አስተዋፅኦ ያደረገዉ በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ መማራቸዉ እንደሆነ መረዳት ተችሏል፡፡

### 4.1.2 ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

**ሰንጠረዥ 5. በመማር ማስተማር ጊዜ የመምህርን የክፍል ውስጥ ተግባር የሚያሳይ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዝቅተኛ | | መካከለኛ | | ከፍተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1 | መምህሯ የትምህርት መርጃ መሳርያ ትጠቀማለች? | 38 | 48.10 | 30 | 35.97 | 12 | 15.18 | | |
| 2 | መምህሯ የቤት ስራ ትሰጣለች? | | | 15 | 18.98 | 45 | 56.96 | 20 | 25.31 |
| 3 | ለንባብ ተነሳሽነት እንዲኖራችዉ ታደርጋለች? | | | 25 | 31.64 | 7 | 8.86 | 45 | 56.96 |
| 4 | መምህሯ ከምንባቡ ለሚወጡ መልመጃዎች በዉይይት እንድትሰሩ ታደርጋለች? | | | 10 | 12.65 | 15 | 18.98 | 55 | 69.6 |
| 5 | ከዚህ በፊት ስላነበባችሁት ምንባብ ስላጋጠማቸዉ ገጠመኝ ሀሳብ እንዲትሰጡ ታበረታታለች ? | | | 23 | 29.11 | 19 | 24.05 | 38 | 48.10 |
| 6. | መምህሪቷ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማወቅ ንቁ ናት? | | | 30 | 37.97 | 23 | 29.11 | 35 | 44.30 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7. | የመምህሪቷ ምንባብ እንድታነቡ ታበረታታለች? | | | 25 | 31.64 | 15 | 18.98 | 20 | 25.31 |
| 8. | ለምትሰሪዉ/ሰራዉ ስህተት ስራ መምህሯ ማስተካከያ ትሰጣለች? | | | 30 | 37.97 | 40 | 56.63 | 10 | 12.65 |
| 9. | መምህሪቷ ለማስተማር ወደ ክፍል ስትገባ ተዘጋጅታ ትገባለች? | | | 26 | 32.91 | 24 | 30.37 | 30 | 37.97 |

ከላይ በሰንጠረዥ ዉስጥ የቀረቡ ጥያቄዎችን በተመለከተ በምእራፍ ሁለት ዉስጥ ሀሳቦች ተቀምጠዋል፡፡ ለምሳሌ Johson (1994) ለማንበብ ትምህርት የሚያገለግሉ የትምህርት መረጃ መሳርያዎችን በማዘጋጀት ምቹ የሆነ አከባቢያዊ የትምህርት አዉድ የመፍጠር ተገቢ ጊዜ የመስጠት ተግባር ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ የምሁራን ሀሳብ አንፃር መምህራን ትምህርትን በሚያስተምሩበት ጊዜ የትምህርት መረጃ መሳርያ በመጠቀም የመማር ማስተማር ዘዴዉን ግልጽ እንዲሆን ያደረገዋል፡፡ ይሄንን መሰረት በማድረግ ለቀረቡላቸዉ ጥያቄዎች በሰንጠረዡ እንደምናየዉ ተማሪዎች የየራሳቸዉን ሀሳብ ሰጥተዋል፡፡

መምህሯ የትምህርት መርጃ መሳሪያ ትጠቀማለች ለሚለዉ ጥያቄ 38 (48.10) ተማሪ ዝቅተኛ፣ 30 (35.97) መካከለኛ፣ 12 (15.18) ደግሞ ከፍተኛ በማለት በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ መምህሯ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ረገድ ያለዉ ነገር አጥጋቢ አለመሆኑን ከሰጡት መልስ ተረጋግጧል፡፡

ሁለተኛዉ ጥያቄ፡ መምህሯ የቤት ስራ ትሰጣለች ለሚለዉ ጥያቄ 15 (18.98) መካከለኛ 45 (56.96) ከፍተኛ 20 (25.31) በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ ከተማሪዎች መልስ የምንረዳዉ መምህሯ በመማር ማስተማር ሂደት ዉስጥ ለተማሪዎች የቤት ስራ በመስጠት ተማሪዎች እንዲሰሩ የምታነቃቃ መሆኑ ነዉ፡፡

ሶስተኛ ጥያቄ፡ መምህሯ ለንባብ ተነሳሽነት እንዲኖራችሁ ታደረጋለች ለሚለዉ ጥያቄ በምእራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸዉ ለምሳሌ Richardሰ (2001) ትክክለኛ የሆኑ ተግባራት በስረዓተ ትምህርቱ ላይ የግበዓት አላማዎችን ተማሪዎች በተግባቦት ሂደት ላይ እንዲሳተፉ እንዲሁም የተግባቦት ሂደት ጠቀሜታ ላይ መረጃ እንዲለዋወጡ እና የቋንቋ አጠቃቀም ብቃታቸዉን እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል ይላል፡፡ ይሄንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ተማሪዎች

የሰጡትን ሀሳብ ስንመለከት 25 (31.64) መካከለኛ 7 (8.86.) ከፍተኛ 45 (56.98) በጣም ከፈተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ መልስ የምንረዳዉ የምንረዳዉ መምህሯ ተማሪ-ተኮር የማስተማር ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት እንዲኖራቸዉ በማድረግ ማስተማሯን ነዉ፡፡

አራተኛ ጥያቄ፡ መምህሯ ከምንባቡ ለሚወጡ መልመጃዎች እየተወያያችሁ እንድትሰሩ ታደርጋለች? ለሚለዋ ጥያቄ በምእራፍ ሁለት ላይ እንደተገለጸዉ ለምሳል ተሻለ (2004) ተማሪ ተኮር ትምህርት አሰጣጥ ሂደት ዉይይት፣ የቡድን ስራ ማካተት አለበት ይላል፡፡ ይሄንን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች ለጥያቄዉ የሰጡትን መልስ ስንመልከት 7 (8.86) መካከለኛ 15 (18.98) ከፍተኛ 55 (69.6) በጣም ከፍተኛ በማለት መመለሳቸዉን ያሳያል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ ተማሪ-ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎች በቡድን እየተወያዩ እንዲሰሩ ማድረጓ ነዉ፡፡

አምስተኛ ጥያቄ፡ ከዚህ በፊት ሰላነበባችሁት ምንባብ ስላጋጠማችሁ ገጠመኝ ሀሳብ እንድትሰጡ ታበረታታለች? በምእራፍ ሁለት እንደተገለጸዉ እንገዳ (1992) Higgins (1984) ዋቢ አድርጎ ማንበብ ዓላማ መወሰንን፣ የምንባቡን መልእክት አስቀድሞ መገመትን፣ የተገመተዉን ግምት ማጣራትን እና የምንባቡን መልእክት ከራስ ገጠመኝ ጋር አዛምዶ ተቀባይነቱን/ ተጨባጭነቱን መገምገምን የሚያጠቃልል ተግባር ነዉ፡፡ ይሄንን የምሁራን ሃሳብ መሰረት በማድረግ በሰንጠረዡ ዉስጥ የቀረበዉን 5ኛ ጥያቄ ስንመለከት 23 (29.11) መካከለኛ 19 (24.05) ከፍተኛ 38 (48.10) በማለት መልሰዋል፡፡

መምህሪቷ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማወቅ ንቁ ናት ለሚለዉ ጥያቄ 30(37.97) መካከለኛ 23(29.11) ከፍተኛ 35(44.30) በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ መምህሯ የማስተማር ሙያዊ ብቃቷ ፅሩ መሆኑን ነዉ፡፡

የመምህሪቷ ንግግር እና ተግባር ይመሳሰላል ለሚለዉ ጥያቄ 25(31.64)መካከለኛ 15(18.98)ከፍተኛ 20(25.31)በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል ተማሪዎች ከመለሱት መልስ የምንረዳዉ መምህሯ ስታስተምር የምትናገረዉእና ተግባሯ ተመሳሳይ መሆኑን ነዉ፡፡

የምትሰራዉ ስህተት መምህሯ ማስተካከያ ትሰጣለች ለሚለዉ ጥያቄ 30(37.97)መካከለኛ 40(56.63)ከፍተኛ 10(12.65) በጣምከፍተኛ በማለት መልሰዋል ከተማሪዎች መልስ

የምንረዳዉ ለትምህረቱ ከተሰጠዉ የክፌለጊዜ ብዛት እና ከተሰጠዉ ደቂቃ አንጻር ለተማሪዎች የምታደርገዉ ጥረት ከፍተኛ መሆኑን እንረዳለን፡፡

መምህሪቷ ለማስተማር ወደ ክፍል በምትገባበት ጊዜ ዝግጁ ሆና ትገባለች ለሚለዉ ጥያቄ 26(32.91) መካከለኛ 24(30.37) ከፍተኛ 30(37.97) በጣም ከፍተና በማለት መልሰዋል፡፡

በአጠቃላይ መምህርቷ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴን በመጠቀም ተማሪዎች ለትምህርት ፍላጎት እንዲኖራቸዉ እተዋጽኦ አበርክታለች ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን አንብቦ መረዳት ችሎታ የሚያሳድግ መሆኑንም ከዚህ እንረዳለን ፡፡

**ሠንጠረዥ 6. ስለ ቅድመ ልምምድ ያላቸዉን ግንዛቤ የሚያሳይ**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎ | ዝቅተኛ | | መካከለኛ | | ከፍተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1 | ከልምምዱ በፊት መምህራችሁ በምንባቡ ዙርያ የቀደመ እዉቀት እንዳለሽ/ህ በመለየት ፍንጭ ይሰጣሉ? | 5 | 6.32 | 30 | 37.97 | 35 | 44.30 | 10 | 1265 |
| 2 | ከልምምድ በፊት ለምን እና እንዴት እንደምታነቡ መምህ ራችዉ ሀሳብ በመስጠት ያበረታቱሽ/ህ ነበር ? | 10 | 12.65 | 10 | 12.65 | 35 | 44.30 | 25 | 31.64 |
| 3 | ምንባብ ለማንበብ ፈላጎት አለሽ/አለህ? | | | 15 | 18.98 | 40 | 50.63 | 25 | 31.64 |

ከልምምዱ በፊት መምህራቸዉ በምንባቡ ዙርያ የቀደመ እዉቀት እንዳለሽ/ህ በመለየት ፍንጭ ይሰጣሉ ለሚለዉ ጥያቄ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡

5 (6.32) ዝቅተኛ፣ 30 (37.97) መካከለኛ፣ 35 (44.30) ከፍተኛና 10 (12.65) በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳዉ በዚህ ጥናት የተዘጋጀዉ የጽሁፍ መጠይቅ

መምህርቷ ከልምምድ በፊት የተማሪዎችን የቀደመ እዉቀት በመለየት ፍንጭ እየሰጠች እንደምታስተምር ነው፡፡

ሁለተኛዉ ጥያቄ፡ ከልምምድ በፊት መምህራችሁ ለምን እና እንዴት እንደምታነቡ ሀሳብ በመስጠት ያበረታቱሽ/ህ ነበር? ለሚለዉ ጥያቄ 10 (12.65) ዝቅተኛ፣ 10 (12.65) መካከለኛ፣ 35 (44.30) ከፍተኛና 25 (31.64) በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ከዚህ ዉጤት የምንረዳዉ መምህሯ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደትን በመጠቀም ተማሪዎች ለምን እና እንዴት ማንበብ እንደለባቸዉ ፍንጭ በመስጠት ማስተማርን እንገነዘባለን፡፡

**ሶስተኛ ጥያቄ** ምንባብ ለማንበብ ፍላጎት አለሽ/አለህ ለሚለዉ ጥያቄ 15(18.98) መካከለኛ 40 (50.63) ከፍተኛ 25(31.64) በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ተማሪዎች ከሰጡትመልስ ከመምህሯ መማር ማስተማር ሂደት አንፃር የምንረዳዉ ተማሪ ተኮር የመማረር ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የማንበብ ፍላጎት የሚያሻሽል መሆኑን ነዉ፡፡

**ሰንጠረዥ 7 በመማር ማስተማር ጊዜ የተማሪዎችን ተግባር የሚያሳይ፡፡**

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | ዝቅተኛ | | መካከለኛ | | ከፍተኛ | | በጣም ከፍተኛ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ | ብዛት | መቶኛ |
| 1 | ምንባቡን መሰረት በማድረ ግ ለምትጠየቂዉ ጥያቄ መልስ ጥሰጫለሽ/ህ? | | | 34 | 43.03 | 20 | 25.31 | 26 | 32.91 |
| 2 | ሃሳብሽን/ህን በነጻነት ትገልፃለሽ/ህ? | | | | | 34 | 43.03 | 42 | 53.16 |
| 3 | ጥሩ ማንበብ ልምድ አለሽ/ህ? | | | 30 | 37.97 | 25 | 31.64 | 25 | 31.64 |

ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለምትጠየቂዉን ጥያቄ መልስ ትሰጫለሽ/ህ ለሚዉ 34(43.03) መካከለኛ 20(25.13) ከፍተኛ 26(32.91)በማለት መልሰዋል በምዕራፍ ሁለት የተገለጸዉን

የTudor (1996).የቋንቋ ትምህርት ገንቢ ሊሆን የሚችለዉ ተማሪዎች በትምህርቱ ሂደት ዉስጥ በንቃት እየተሳተፉ እዉቀታቸዉን እና እምቅ ችሎታቸዉን ከነበራቸዉ ልምድ ጋር እያዋሀዱ በራሳቸዉ ጥረት ሲማሩ ነዉ፡፡ የሚለዉን የምሁሩን ሀሳብ መሰረት በማደረግ ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቅ  የሰጡትን መልስ ስናይ በዚህ ጥናት ዉስጥ የተደረገዉ የመማር ማስተማር ሂደት  የተማዎችን በንቃት በመሳተፍ መማርን  እንረዳለን፡፡

ሀሳብሽን/ህን በነጻነት ትገልጻለህ ለሚለዉ ጥያቄ ተማሪዎች የየራሳቸዉን መልስ መልሰዋል፡፡ መልሳቸዉም 34 (43.03) ከፍተኛ 42(53.16) በጣም ከፍተኛ በመለት መልሰዋል በዚህ ጥናት ዉስጥ የተዘጋጀዉ የፅሁፍ መጠይቅ ተማዎች ሀሳባቸዉን የለምን ፍራቻ እንደሚገልፁ እንረዳለን ሀምዕራፍ ሁለት piaget (1938) ተማሪዎች አዲስ ልምዶችን እና ግኝቶችን በማሰተባበር በእዉቀትና በማስታወሻ መንገድ ያለ ፍራቻ እየገለፁ እንዲገነዘቡ ያደርጋል ካሉት ሀሳብ ተደጋጋፊ ነዉ፡፡

ጥሩ ማንበብ ልምድ አለሽ/ህ? ለሚለዉ ጥቄ 30(37.97) መካከለኛ25(31.64) ከፍተኛ እንዲሁም 25(31.64) ተማሪዎች በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡

ከዚህ መልስ የምንረዳዉ የማንበብ ችሎታቸዉ ጥሩ እንደሆነ እንረዳለን፤በአጠቃላይ ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘዉን  መረጃ መሰረት በማድረግ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ የተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ማሻሻሉን ነዉ፡፡ መሻሻሉንም የሚያሳይ ተማሪዎች ምንባብ ለማንበብ ያላቸዉን ፍላጎት ከግምት ዉስጥ በማስገባት እና የሁለቱም ቡድን ድህረ ፈተና ዉጤት በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ በመማር ዉጤታቸዉ መሻሻሉን ነዉ፡፡

## 4.2 የዉጤት ማብራሪያ

ጥናቱ ትኩረት ያደረገዉ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉን አስተዋፅኦ መመርመር ነዉ፡፡ይሄንን አላማ ከግብ ለማድረስ የጥናቱን መሰረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ እንዲረዳ ጥናቱ ከሚካሄድበት ቦታ ከሚገኙ የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል፡፡

በበፈተና እና በጽሁፍ መጠይቅ መረጃ መሰረት  ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ/ነጻ ተለዋዋጭ; በተማሪዉ አንብቦ መረዳት ችሎታ /ለጥገኛ ተለዋዋጭ/ አስተዋፅኦ ማድረጉን

ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘዉ ዉጤት ወደ መቶኛ በመቀየር የተተነተነ ሲሆን በፈተና የተገኘ የተማሪ ዉጤት ደግሞ መደበኛ ልይይት ፣ልይይት እና አማካይ ዉጤት በ spss መረጃ መተንተኛ ሶፍት ዌር በመጠቀም በባፅድ ናሙና ቲ-ቴስት ተተንትኗል፡፡ጥናቱ እንዲመልስ የታሰበዉ ጥያቄ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉን አሰተዋፅኦ የሚል ነዉ፡፡ ጥያቄዉንም ለመመለስ በፈተና እና በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበዉን መረጃ እንደሚከተለዉ ተተንትኗል፡፡

የጥናቱ አላማም ተማሪዎች ያላቸዉን የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመፈተሽ ለሙከራ ቡድን ቅድመ እና ድህረ ፈተና ለቁጥጥር ቡድን ቅድመና ድህረ ትምህርት ፈተና ተሰጥቶ በረዳት መምህሯ ታርሟል፡፡ በዚህ መሰረት በቁጥጥር እና በሙከራ ቡድን በቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ችሎታ መካከል ልዩነት አለመኖሩ ማለትም ተቀራራቢ የሆነ ዉጤት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

የሁለቱ ቡድን ቅድመ ትምህርት ፈተና ከመደበኛ ልይይት (3.728) ከልይይት (7.457) ከአማካይ ዉጤት (24.25) ለማየት ተችሏል፡፡ ይህ የቅድመ ትምህርት ፈተና ዉጤት ሲሆን ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለዉ ዉጤቱ ያመለክታል፡፡ የድህረ ትምህርት ፈተና ዉጤት መደበኛ ልይይቱ (2.636) አማካይ ዉጤቱ (28.85) እና ልይይቱ (5.272).በተመለከተ ከቅድመ ትምህርት የአንብቦ መረዳት ፈተና ይልቅ ድህረ ትምህርት አንብቦ መረዳት ፈተና በልጦ ተገኝቷል፡፡ ስለዚህ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ በራሳቸዉ ፍላጎት/ተነሳሽነት ለማንበብ ያላቸዉ

ዉስጣዊ ተነሳሽነት የጎላ ስላደረገዉ ካነበቡም በኂላ ጥሩ ዉጤት ስላስመዘገቡ ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለዉ፡፡

ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለዉ ከሚሉ ከAnderson(1999) Jones(2007) የጥናቱ ዉጤቶች ጋር የሚስማሙ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡

ተማሪዎች የማንበብ ጉጉት እነዲኖራቸዉ በመማሪያ መፅሀፍት ዉስጥ ቀልብን የሚስቡ /የሚመስጡ ምንባቦች ቢገቡ፡፡

- ሁሉም መምህር ሁሌም ተማሪ ተኮር የመማር ማስተመር ዘዴን ቢጠቀም፡፡
- የመማርያ ቁሳቁሶች ከቴክኖሎጂ ጋር የተራመዱ ቢሆኑ፡፡
- ይህን ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት በመጠቀም ሌሎች ጥናቶች ቢካሄዱ ጥሩ ነዉ፡፡
- መምህራን ብዙ ጊዜ ይሄንን የመማር ማስተማር ስልጥ ሲጠቀሙ አይታይም ምክንያቱም ካለዉ ጊዜ አንጻር ሁሉን ተማሪ ማሳተፉ ስለሚከብድ መምህራን ብዙም ሲጠቀሙት አይታይም አንድ መምህር /ተመራማሪ ምርምር ሲያካህድብቻ ባንጠቀም ጥሩ ነዉ፤ ይህ ማለት ቀረፃሲኖር ለዝያ ቀረፃ ተብሎ ባይሰራ ጥሩ ነዉ ፡፡

# ምዕራፍ አምስት
# 5. ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት አላማ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ ያለዉን አስተዋፅኦ መፈተሽ ነዉ፡፡

ይሄንን ጥናት ለማሳካት ፈተና እና የፅሁፍ መጠይቅ  መረጃ መሰብሰብያ ሆነዉ አገልግለዋል፡ ፡ በዚህ ጥናት ዉስጥ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ሂደት ለተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረግ አለማድረጉን ለማረጋገጥ ለተጠኝዎች የቅድመ እና ድህረ ትምህርት ፈተና ለማካሄድ በተመረጡ ለሁለቱ ቡድኖች  ተሰጥቶ ዉጤታቸዉ  በባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ፤  በቅድመ ትምህርት ፈተና ላይ ብዙም ጉልህነት እንደሌለዉ እና በድህረ ትምህርት ፈተና ላይ ግን ጉልህነት እንዳለዉ ባዕድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ሌላዉ ለተማሪዎች ከቀረቡላቸዉ የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘዉ  ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ስልት ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ጥሩነትን እንዳለዉ ከሰጡት መልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡ አንብቦ መረዳት ችሎታን  ለማሳደግ ለተማሪዎች የሚመጥኑ ምንባቦች መርጦ ተማሪ ተኮር በሆነ መንገድ ማዘጋጀት ቢቻል ተማሪዎች ቀስ በቀስ ትምህርታቸዉን በራሳቸዉ የመምራት አቅም ማጎልበት እንደሚችሉ ያስረዳል፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ መረጃ መሰብሰብያ ሆነዉ ካገለገሉ ከፈተና እና ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ አስተዋፅኦ ማድረጉን በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡

## 5.2 አስተያየት

አጥኚዋ ከጥናቱ ግኝቶች በመነሳት የሚከተሉትን አስተያቶች ሰጥታለች፡፡

መምህራኑ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለማሳደግ ተማሪዎች የተለያዩ መጽሀፎችን በማንበብ  መልእክቱን በክፍል ዉስጥ በማቅረብ ቢያነቡ፡፡

በእንግሊዘኛ ትምህርት የንግግር ጊዜ ተብሎ እንደሚሰጠዉ በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜም የንባብ ክፍለ ጊዜ ቢመቻች፡፡

መምህራን መልመጃዎችን በሚሰጡበት ጊዜ አንብበዉ ከተረዱት በኋላ የሚመለስ ወይም የአንብቦ መረዳት ጥያቄ ቢሰጡ፡፡

ወደፊት ከተማሪ-ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ጋር ተያያዥነት ያለዉ ምርምር ቢካሄድ ጥሩ ነዉ፡፡

መምህራን በተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ስልት ምንባብን ሲያስተምሩ የትምህርት መርጃ መሳርያን በአግባቡ ቢጠቀሙ፡፡

ተማሪዎች የማንበብ ጉጉት እነዲኖራቸዉ በመማሪያ መፅሀፍት ዉስጥ ቀልብን የ/የሚመስጡ ምንባቦች ቢገቡ፡፡

ሁሉም መምህር ሁሌም ተማሪ ተኮር የመማር ማስተመር ዘዴን ቢጠቀም፡፡

የመማርያ ቁሳቁሶች  ከቴክኖሎጂ ጋር የተራመዱ ቢሆኑ፡፡

ዋቢ ፅሁፎች

ማስተዋል ዉበቱ። (1989)። የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ የአንብቦ መረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችየ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት።

ሰለሞን አመንቴ። (2001)። ተማሪ-ተኮር የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አቀራረብ በቦጅ ጮቆርሳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት። ጅማ ዩኒቨርሰቲ።

ተስፋዬ ወልደሚካኤል። (2001)። የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ አ.አ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት ያልታተመ አ.አ ዩኒቨረሲቲ።

አለም እሼቱ።(1999)። መሰረታዊ የምርምር ዘገባ አጻጻፍ አዲስ አበባ ንግድና ማተምያቤት

አስቴር አስራት። (2010)። ንባብን አንብቦ መረዳትና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲተ፣የቋንቋጥናት ተቋም ለ10ኛ አመት የቋንቋ ጥስፖዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ።

እቴነሽ በቀለ። (2010)።በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች የማንበብ ልምድእና የአንብቦ መረዳት ተዛምዶ። በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት።ለሁለተኛ ድግሪ መሟሚያ ቀረበ ጥናት ጎንደር ዩኒቨረሲቲ።

አንድነት እርጉ ።(2010)። በባቶ ሙሉ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላይ ከላይ ታች እና ከታች ላይ የማንበብ ትምህርት ማስተማሪያ ሞዴል በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ መረዳት ክህል ላይ ያላቸውን አስተዋጽኦ በማነጻጸር የተቻለውን ሞዴል ለመለየት 7ኛ ክፍል ተማሪዎችን ተተኳሪ ያደረገ።

እንገዳ ዘዉዴ። (1992)። ቶፐ ዳዎን የንባብ ማስተማርያ ሞዴል በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታን ለማዳበር ያለዉ ተግባራዊነትና ዉጤታማነት በ9ኛ ክፍል ተመርዎች የተካሄደ ጥናት አዲሰ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለማስተማር ድግሪ ማሚያ(ያልታተመ)።

አደይ ብርሀኑ። (2011)። የአማርኛ አቀላጥፎ ማንበብ ከአንብቦ መረዳት ችሎታጋር ያለዉ ተዛምዶ፡ በአራተኛ ክፍል አማርኛ አፈ-ፈት ተማሪዎች ተተኳሪነት።

አዳነ ሽፈራዉ።(2001)። ተማሪ ተኮር አቀራረበብ በአሙሩ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፡ በአስረኛ ክፍል በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ።

የማርያምወርቅ አበበ። (2013)። የመደገፍ ብላሃቶች የተማሪዎችን አንብቦ መረዳትና የማንበብ ተነሳሽነት ለማደበርያላ ሚና በ9ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት።

ያለዉ እንዳወቅ። (2001)። ምርምር መሰረታዊ መረሆችና አተገባበር፡አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት:: የቋንቋዎች ጥናት የጋዚጠኝነትና ኮሚኒኬሽን ኮላጅ ::

ዳዊት ደስታ።ማንበብ ሙሉ ሰዉ ያደርጋል። አዲስ አበባ።

ፋሲካ ዉበቱና አገኘሁ ትስፋ። (2010)። በትብብር መማር አንብቦ መረዳት ችሎታና ፍላጎት ላይ ያለዉ ሚና በ11 ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት።

Afar national rgion state Education bureau(2012).

Anantasa, G. and Kemuning, S. M. (2016). Gender difference in reading comprehension achievement: A case study. ELT. 45 (1).

Andrson, N. S. (1999). Improving reading speed activites for classroom. www.englishteaching.com

Anni, Trembly.(2011). Students in second language acquision.Urban, champing.

Brendes, D. and Ginnes, P. (1986). A guide to student-centerd learning. London: Simon and Chuster Education.

Brown, D(2007). Principle of Language Lerning and Teaching. New York: Longman.

Campbel, M. (2001). Fromework and specifications for PIRLS assessment (2nd ed.). Chestnut Hill, MA: Boston College.

Davies, F. (1995). Introducing reading. Cambrige: Cambrige University Press.

Ephram, K. (2009). Reading comprehension inststruction. Liberty University.

Fry, E. (1963). Readig faster. A drill books. Cambrige: Cambrige University Press.

Ginnin, T. G. (2013). Creating literacy instruction for allchildren in grades pre-kindergraton to

Grellent, F. (1981). Developed reading skills apractical guide to reading comprehension execice. New York: Cambridge University Press.

Green hold J.(1988) class readers oxford.oxford university.pyess.

Harmer, J. (1991). The practice of English language teaching. London: Logman.

Hilgar, E. and Bower, G.H . (1966). Theories of learning. New York: AP Pilton.

Hill.(2011).in examination of second language reading research and implication for English language teaching practice the Arbtas reviw vol. 2 (Nol)

Hockett, E. (1959). Objective and process of languge theching reprited.

Hughes, A. (1989). Tessing language Teachers Cambrige. Cambrige: Cambrige University Press.

Johnes, L. (2007).The student centerd–classroom. Cambridge: Cambridge University Press.

Johnson,D.W. and Jhnson, R.T. (1994). Cooperative learning in the classroom.

Kuhan.et.al. M.Rand levy .L(2015).what if ffuent reading new york.Goit ford.

McCombs, B. and Whistler, J. S. (1997). The learner-centerd classroom and school: Strategies for increasing student motivation and achievement. San Francisco: Jossey Bass Publishers.

Mothes L.c.L (1999). Teaching Reading is rocket scince What exertteachers ofreading should know and able to do Texas Houstion Health Sicince center.

Natall, C. (1996). Teaching reading skills in foreign language. Heinemenn education books.

Nunan, D. (1938). The learner-center curriculum: A study in second language teaching. Cambridge: Cambrige University Press.

Pearson, D., Roehler, L., Dole, J. A. and Duffy, G.G. (1992). Developing Experties in Reading Comprehension.

Person, D. (2009). Historical perspective on reading comprehension: The roots of Reading comprehension instruction. Hand book of Research on reading.

Pikulski, J. and Chard, D. J. (2005). Fuency: Bridge between de-coding and reading, comprehension. The Reading Teacher, 56 (6), 510-519.

Piper, B.(2010). Ethiopia early grade reading assessment:data analtic report. Journal of Adolescent and Adult, 54, 22-27.

Rant Nuke,(2012 Approaches in language testing national che kung university.

Richard, J. and Rodgers, T.S. (1986). Approach and method in language teaching (1st. ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Richard, J. and Rodgers, T.S. (2001). Approaches and methodse in language teaching (2nd ed.). Cambridge: Cambridge University Press.

Sheng, H. J. (200). Cognitive Model for teaching Reading Comperhension. English Teaching Forum, 38 (4),12-15.

Simith, F. (1978). Reading cambredge. Cambridge: university press.

Snow,C.E.and sweet,A.P.(2003).reading for comprehension. In A.P sweet and C.E.

Snow (Eds). Rethinking Reading Comprehension (pp.1-11).new york:Guilfofd press.

Stern,H.H(1938).Fundamental conceptof Language Teaching. Oxford:oxford university press.

Tundor.l.(1996).Basic principies of curriculum and innovation. Chicago; Chicago university press.

.

## አባሪ 1



የሙከራ ቡድን የንባብ ጊዜ ትግበራ



**የቁጥጥር ቡድን የንባብ ጊዜ ትግበራ**

# አባሪ 2

**results before**

| | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 21 | 1 | 2.5 | 2.5 | 2.5 |
| | 23 | 1 | 2.5 | 2.5 | 5.0 |
| | 24 | 2 | 5.0 | 5.0 | 10.0 |
| | 25 | 1 | 2.5 | 2.5 | 12.5 |
| | 26 | 2 | 5.0 | 5.0 | 17.5 |
| | 27 | 3 | 7.5 | 7.5 | 25.0 |
| | 28 | 7 | 17.5 | 17.5 | 42.5 |
| | 29 | 5 | 12.5 | 12.5 | 55.0 |
| | 30 | 9 | 22.5 | 22.5 | 77.5 |
| | 31 | 1 | 2.5 | 2.5 | 80.0 |
| | 32 | 3 | 7.5 | 7.5 | 87.5 |
| | 33 | 4 | 10.0 | 10.0 | 97.5 |
| | 34 | 1 | 2.5 | 2.5 | 100.0 |
| | Total | 40 | 100.0 | 100.0 | |

**results before**

| | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 19 | 1 | 2.5 | 2.5 | 2.5 |
| | 20 | 5 | 12.5 | 12.5 | 15.0 |
| | 21 | 2 | 5.0 | 5.0 | 20.0 |
| | 22 | 4 | 10.0 | 10.0 | 30.0 |
| | 23 | 4 | 10.0 | 10.0 | 40.0 |
| | 24 | 6 | 15.0 | 15.0 | 55.0 |
| | 25 | 5 | 12.5 | 12.5 | 67.5 |
| | 26 | 4 | 10.0 | 10.0 | 77.5 |
| | 27 | 1 | 2.5 | 2.5 | 80.0 |
| | 28 | 5 | 12.5 | 12.5 | 92.5 |
| | 29 | 1 | 2.5 | 2.5 | 95.0 |
| | 30 | 2 | 5.0 | 5.0 | 100.0 |
| | Total | 40 | 100.0 | 100.0 | |

**Result after**

| | | Frequency | Percent | Valid Percent | Cumulative Percent |
|---|---|---|---|---|---|
| Valid | 22 | 1 | 2.5 | 2.5 | 2.5 |
| | 23 | 1 | 2.5 | 2.5 | 5.0 |
| | 26 | 1 | 2.5 | 2.5 | 7.5 |
| | 28 | 2 | 5.0 | 5.0 | 12.5 |
| | 29 | 5 | 12.5 | 12.5 | 25.0 |
| | 30 | 8 | 20.0 | 20.0 | 45.0 |
| | 32 | 4 | 10.0 | 10.0 | 55.0 |
| | 33 | 7 | 17.5 | 17.5 | 72.5 |
| | 34 | 6 | 15.0 | 15.0 | 87.5 |
| | 35 | 3 | 7.5 | 7.5 | 95.0 |
| | 36 | 2 | 5.0 | 5.0 | 100.0 |
| | Total | 40 | 100.0 | 100.0 | |

**Posterior Distribution Characterization for One-Sample Mean**

| | | Posterior | | | 95% Credible Interval | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | N | Mode | Mean | Variance | Lower Bound | Upper Bound |
| results before | 40 | 24.25 | 24.25 | .248 | 23.27 | 25.23 |
| Result after | 40 | 31.30 | 31.30 | .283 | 30.25 | 32.35 |

Prior on Variance: Diffuse. Prior on Mean: Diffuse.

**Posterior Distribution Characterization for Binomial Inference[a]**

| | Posterior | | | 95% Credible Interval | |
|---|---|---|---|---|---|
| | Mode | Mean | Var. | Lower Bound | Upper Bound |
| results before | .071 | .091 | .002 | .026 | .191 |
| Result after | .071 | .091 | .002 | .026 | .191 |

a. Prior on Binomial proportion: Beta(2, 2).

**Correlations**

| | | | results before | Result after |
|---|---|---|---|---|
| Kendall's tau_b | results before | Correlation Coefficient | 1.000 | .942** |
| | | Sig. (2-tailed) | . | .000 |
| | | N | 40 | 40 |
| | Result after | Correlation Coefficient | .942** | 1.000 |
| | | Sig. (2-tailed) | .000 | . |
| | | N | 40 | 40 |
| Spearman's rho | results before | Correlation Coefficient | 1.000 | .981** |
| | | Sig. (2-tailed) | . | .000 |
| | | N | 40 | 40 |
| | Result after | Correlation Coefficient | .981** | 1.000 |
| | | Sig. (2-tailed) | .000 | . |
| | | N | 40 | 40 |

**. Correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

**One-Sample Statistics**

| | N | Mean | Std. Deviation | Std. Error Mean |
|---|---|---|---|---|
| results before | 40 | 24.25 | 2.985 | .472 |
| Result after | 40 | 31.30 | 3.188 | .504 |

**One-Sample Test**

| | Test Value = 0 | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | 95% Confidence Interval of the Difference | |
| | T | Df | Sig. (2-tailed) | Mean Difference | Lower | Upper |
| results before | 51.380 | 39 | .000 | 24.250 | 23.30 | 25.20 |
| Result after | 62.093 | 39 | .000 | 31.300 | 30.28 | 32.32 |

# አባሪ 3

የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1.ክርክር ማለት ምን ማለት ነዉ

2.ክርክር ተከራከራችዉ ታዉቃላችሁ

3.አንድ ተከራካሪ ክርክር ዉስጥ ከመግባቱ በፍት ምን ማድረግ አለበት

## ክርክር

ክርክር ማለት በሁለት ሰዎች ወይም በሁለት ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት ነዉ፡፡

በህብረተሰባችን በስፋት የተለመደ ሲሆን፡ ሲተገበርም በርካታ አመታት ንአስቆጥሯል ይሁን እንጂ ለአሸና ፊነት የሚደረገዉ ትግልና በአንዳድ ሌሎች ነጥቦች ቢመሳሰሉም የጥንቱ ሙግት ናየዛሬዉ ክርክር ሰፊ ልዩነት አላቸዉ፡፡ በሀገራችን ልዩልዩ አካባቢዎች ያሉ ባህላዊ የሙግት ስረዓቶችም እንደዚሁ ይለያያሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ጥንት የሰሜን እና በመካከለኛዉ የሀገራችን ክፍል ይተገበር የነበረዉ‹‹እስጥአገባ›› ወይም ሙግት እንደምሳሌ እንመለከታለን፡፡

ዳኛወይምሽማግሌዎችበዛፍስርወይምበሜዳላይይቀመጣሉ፡፡

በፍቃዳቸዉወደችሎትያመጣሉታዳሚዎችም እንደዚሁ እርስበርስ በመከባበር፡ ለእድሜ ባለጸጎች ና ለሽማምንቶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸ ዉ ቦታቸዉን ይይዛሉ፡፡በኋላ ላይም የፍርድ ትችት ሰይሰጣል፡፡

ሙግት ሲጀምር ከሳሽ በቀኝ ተከሳሽ በግራ ይቀመጣሉ፡፡ ሁለቱም አንዳንድ እማኝ ይመርጡና እማኞቹ በበኩላቸ ዉየመሀልዳኛ ይሰይማሉ፡፡በመቀጠል ከሳሽና ተከሳሽ የስረዓት.(ስነስረዓት) ዋስይጠራሉ፡፡ዋሶችመሓላ ከፈፀሙ በኋላም ክርክሩ ይቀጥላል፡፡

ከሳሽና ተከሳሽ እጀጠባብ ናሱሪ ለብሰዉ ፡ኩታቸዉን አደግድገዉ ይቀርባሉ፡፡ (ማደግደግ ማለት ኩታ ወይም ሽማ በትክሻ ዞሮ ወገብ ላይ ይጠመጠምና የኩታዉን አንዱን ጫፍ በቀኝ ወይም በግራ ትክሻ ማዉረድ ነዉ)፡፡ከሳሽ ‹‹እግዚያብሔር ያሳየዎ!፡፡ በሚል መግብያ ክሱን ሰይደረድራል፡፡

ተከሳሽ የቀረበበትን ክስ የካደ እንደሆነ፡ ከሳሽ ሳርርዱን በማስቀመጥ ‹‹በርታ! ፡ነጭማር፡ ነጭፈረስ፡ ሰጋርበቅሎ፡ ሰንጋ ወይም ሙክት  እስጥ---›› በማለት ፡ዘንጉን በግራ እጁ ጨብጦ፡ የቀኝ እጁን አመልካችጣት ወደዳኛ ቀስሮ፡  ከፊት ወደኋላ ካፈገፈገ በኋላ፡ ክሱን ይደረድራል፡ ፡ ተከሳሽም ተመሳሳዩን ያደርጋል፡፡

ከዚያ ብይንይሰጣል፡፡ለምሳል፡ላምየጠፋበትሰዉ‹‹አርዶበልቷል›› ብሎ ከጠረጠረዉ ሰዉ ጋር ሲከራከሩ አለ የተባለዉን ና የተከሳሹንም ምላሽ በምሳሌነት እናንሳ፡

ከሳሽ፡- ላሜጠፍታከደጋ

ስከተልመጣሁበደምፍለጋ

ብድረስበፍለጋከደጅህ

ሙዳስጋይዟልልጅህ

ስለዚህላሜንትከፍላለህ፡፡

ተከሳሽ፡-ላምህብትጠፋ ከደጋ

አንተም ብትመጣ ፍለጋ

ከቤቴ በላይ አለ ተራራ

መዘዋወርያዉ የጅብ ያሞራ

ከቤቴ በላይ ዛፍ አለ

በዛፉም አሞራ ያርፋል

በመንገዱም ጅብ ይሄዳል፡፡

አሞራናጅብሲጣለፉ

ሙዳ ስጋ ቢተፉ

ነብስ ያላወቀ ልጅ ቢያነሳ

አያስከፍለኝም ነገርህን አትርሳ

ዉርርድህን አንሳ

በዚህ መልኩ ሙግቱ ተካሂዶ ዳኞች ግራቀኙን አዳምጠዉ በአማኞች ትችትና አሰተያየት ተደግፈዉ። በለተከሳሽመልስዋጋበመስጠት፡ከሳሽን ተራች አደረጉ ይባላል።

### የንባብ ጊዜ ትያቄዎች

1 የምንባቡና ከዚህ ቀደም የምታዉቁት ክርክር ሂደቱ አንድነዉ

2.እስካሁን የተረዳችሁት ነገር ምንድነዉ

3.ክርክር ለምን ይካሄዳል

በአመናችን ክርክር በከሳሽና በተከሳሽ መካከል ብቻ የሚደረግ አይደለም። በሌሎች ዘርፎች በስፋት ካሄዳል።ለምሳሌ ፖለቲከኖች፣ አንዱ ቡድን የራሱን አቋም በመደገፍ ሌላዉን በመቃወም ይከራከራሉ። ህዝብ ዳኛ የይሆንና ፍረድ ይሰጣል። በፈራጅ ድምጽ መሰረት አንዱ ባለድል ሌላዉ ተረቺ ይሆናል።

በተማሪዎች መካከልም እነዲሁ በተቃራኒ ሀሳቦች ዙርያ ክርክሮች ይካሄዳሉ። ተማሪዎች የሚያካሂዷቸዉን እነዚሁ ክርክሮች ዘርዘር አድረጎ መመልከት፣ስለዘመኑ ክርከር መልካም ግንዛቤ ያስችብጣል። የክርክሮቹን ሂደትም  የዝግጅትና የክርከር ጊዜ ተግባራት በማለት በሁለት ደረጃ ከፍሎ ማየት ይቻላል። ብዙዎቹ ጥሩ ተከራካሪ የሚባሉት፣ በዝግጅት ወቅት በቅድሚያ  የመክራክር ያ ርዕሱን  የሚመለከቱ  ሀሳቦችን  ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ይቃርማሉ። ይህም ባለሙያዎችን በማነጋገር ወይም ጽሁፎችን በማንበብ፣ ከስፈለገም ሁለቱንም መንገዶች በመጠቀም ሊሆን ይችላል።

መረጃዎችን ከሰበሰቡ በኂላ፣ይበልጥ ተቃሚ የሆኑትን በቅደም ተከተል በማደራጀት፣ በአጭሩ በትንሽ ወረቀት ላይ በማስታወሻ መልክ ያሰፍራሉ። ይሄንን ማድረጋቸዉ፣ ላይ ታች ከመርገጥ ያድናቸዋል። ተከራካሪዎች  በየፊናቸዉ ለሚከራከሩበት ርእስ  ጉዳይ የሚሆኑ መረጃዎችን ከሰበሰቡና  ማስታወሻቸዉን ካደራጁ በኂላ፣ ቀጣዩ ስራቸዉ ልምምድ ይሆናል። ልምምድን የሚያካሂዱት በሁለት መንገድ ነዉ። አንደኛዉ በየግል በመስታዎት እራሳቸዉን እያዩ መለማመ ድሲሆን ፣ ሁለተኛዉ ደግሞ ሌሎች ሰዎች ልምምዳቸዉን አይተዉ

አስተያየት እንዲሰጧቸዉ  በመድረግ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ዝግጅት ካጠናቀቁ በኂላ ወደ ዋናዋናዎቹ  የክርክር መድርግ ተግባራት ይገባሉ፡፡ ተከራካሪዎች  ክርክራቸዉን የሚጀምሩት

ሰላምታ በመስጠትና ርእሳቸዉን በማስተዋወቃቸዉ ነዉ፡፡ አያይዞም በተቀመጠዉ የሀሳብ ቅደም ተከተል እየተመሩ የክርክር  ነጥባቸዉን ያቀርባሉ፡፡ ለዚህ አካሄዳቸዉ ማስታወሻ የያዙበት ትንሽ ወረቀት፣ ትልቅ ድረሻ አላት፡፡ ክርከራቸዉን በወጉና በራስ የመተማመን መንፈስ  ለማቅረብ ትረዳቸዋለች፡፡ እዚህ ላይ በራስ  መተማመን የሚፈተረዉ በቂ ዝግጅት ከማድረግ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል፡፡ ከተቃዋሚ ወገን ሚቀርቡ አስተያየቶችን በጥሞና በማዳመጥ ማስታወሻመያዝም፣ ሌላ ጠቃሚ ተከራካርዎች ተግባር ነዉ፡፡

ይህ የሚሆነዉ ለተዘረዘሩት ትችቶች ና መቃወሚያዎች አፍራሽ  ሀሳቦችን ለመስጠት ስለሚጠቅም ኑዉ፡፡ አስፈላጊ እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ መቆጠብ፣ ድምጽን ለታዳሚዎች በሚሰማበት መጠን መመጠን ና እይታን ወደ አድማጮች ማድረስ ሌሎች የትኩረት  ነጥቦች ናቸዉ፡፡ጥሩ ተከራካሪዎች ከለይ በተጠቀሱት ተግባር ብቻ  አይበቁም፡፡ ለመከራከርያ የሚያነሷቸዉ ፍሬ ሀሳቦች፣ በአተቃላይ ክርከራቸዉ ፣ አድማጮቻቸዉን  የሚስብ፣ የአድማጮቻቸዉን ችሎታ ያገናዘበ ና  የተከራካሪዎችን ስብዕና የማይነካ፣ ማለትም ቅር የማያሰኝ፣ መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡ ትግሉ ከተከራካሪዎች ጋር ሳይሆን ፣ ከሀሳቡጋር መሆኑን ያሳዉቃሉ፡፡ ንግግራቸዉ ከተሰጣቸዉ ጊዜ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ይጥራሉ፡፡ ከርእሳቸዉ እንዳይወጡ ይጠነቀቃሉ፡፡ ሌላዉን ወገን ሳያከብሩ መከበርን መናፈቅ አይቻልም፣ ለተከራካሪና ለአድማጮች እንዲሁም ለዳኞች አክብሮትን አይነፍጉም፡፡ ክርክራቸዉን አተቃለዉ ሲሰናበቱም ሁሉንም ታዳሚዎች ያሰናብታሉ፡፡ የዳኞች ዉሳኔ ምንም ይሁን ምን በጸጋ ይቀበላሉ፡፡

## አባሪ 4

## ለ9ኛክፍል የተዘጋጀ የአነረብቦ መረዳት ፈተና

## ጅማ ዩኒቨረሲቲ

## የአማርኛ ቋንቋ ስነ -ጽሁፍ  አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድህረ ምረቃ መረሃ ግብር

**ይህ አንብቦ መረዳት መለክያ ፈተና የተዘጋጀዉ ተማሪ ተኮር ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ፈተና ያለዉ አሰተዋጽኦ በሚል ርእስ ለሚሰራዉ ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡ ለዚህ ከዚህ በታች የቀረበዉን ምንባብ  መሰረት በማድረግ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጡ፡፡**

፩.የሚከተሉትን ጥያቄዎች ትክክል ከሆኑ እዉነትካልሆኑ ሀሰት በማለት መልሱ፡፡

1.ክርክርማለት በሁለት ሰዎች መካከል የሚከወን የቃል ምልልስ ማለት ነዉ፡፡

2.ክርክር ሲካሄድ በተከራካሪዎች መካከል ግጭት አይጠፋም፡፡

3.ክርክር ለማካሄድ መጀመርያ የክርክሩን ርዕስ መመረጥ አለበት፡፡

4. ክርክርና ዉይይት ባሕሪያቸዉ አንድ ነዉ፡፡

5.ስረዓት ያለዉ ክርክር ለማካሄድ የተከራካሪዎች መደማመጥ አስፈላጊ አይደለም፡፡

6. አከራካሪዉ /መሪዉ/ የክርክሩን ነጥብ መግለፅ አያስፈልገዉም፡፡

7.ክርክር እና ሙግት የተለያዩ ነገሮች ናቸዉ፡፡

8.በቡድንም ሆነ በግል የሚከራከሩ ሰዎች በመሀላቸዉ የሚከታተላቸዉ ሰዉ መኖር አለበት፡፡

9.ክርክር ስለ አንድነገር ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረን ያደርጋል፡፡

10.ክርከር ከሚለዉ ቃል ክር የሚል ቃል መመስረት ይቻላል፡፡

፪.በ‹‹ሀ›› ረድፍለ ቀረበዉ ቃል በ‹‹ለ›› ስር ከቀረበዉ ተመሳሳይ ፍቻቸዉ ጋርአዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 11.ታዳሚ | ሀ.ስም ማዉጣት |
| 12.ሙጎት | ለ.በእድሜ የገፋ |
| 13.ብይን | ሐ.ተሳታፍ |
| 14.ኩታ | መ.ዉሳኔ |
| 15.ሽማግሌ | ሠ.ቀጭን የብረት ዱላ |
| 16.መሰየም | ረ.የጥጥ ዉጤት/ወፍራም ጋቢ |
| 17.ዘንግ | ሰ.መገንዘብ |
| 18 ድልማድረግ | ሸ.ክርክር |
| 19.ፀጋ | ቀ.ማሸነፍ |
| 20.ማጤን | በ.ስጦታ |

፫.ከሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ በመምርጥ መልሱ፡፡

1. ክርከርከ ከተካሄደ በኋላ በመጨረሻ መሆንያለበ ነገር የቱነዉ;

ሀ. ዉሳኔ መስጠት ለ.ተከራካሪዎችን መምረጥ ሐ. መሰብሰብ መ. ዳኛመምረጥ

2.ክርክር በሚካሄድበት ጊዜ ተከራካሪዎች

ሀ.ማስታወሻ መያዝ የግድ ነዉ ለ.ማዳመጥ አለባቸዉ ሐ.በሃሳብ ላይ መጣላት አለባቸዉ መ.መልስየለዉም

3.ክርክር ሲካሄድ ፆታን ያማከለ መሆን አለበ.

ሀ.እዉነትለ . ሀሰት

4.ተከራካሪዉ ክርክሩን ለማሸነፍ፡-

ሀ.ሀሳቡን ግልፅ ማድረግ አለበት፡፡ ሐ.ጉልበታም መሆን አለበት

ለ.ተናጋሪ መሆን አለበት መ.ታዋቂ መሆን አለበት

5.ክርክር የተከራካሪዎችን--------------ይጨምራል፡፡

ሀ.በራስ መተማመን ለ.ዉበት ሐ.በርእሱ ላይ ያላቸዉን ቸሎታ መ.ሀናሐ

6.ክርክር ከሚለዉ ስንት ቃል ይመሰረታል

ሀ2 ለ.1 ሐ.4 መ.

7.ክርከር ምንን ያመለክታል?

ሀ.መዋደድን .ለ.ፀብን ሐ.ፍቅርን መ.በአንድ ሀሳብ ላይ አለመስማማትን

8.የመከራከሪያ ርዕሱ የሚመረጠዉ?

ሀ.በተከራካሪዎች ነዉ ለ.በሽማገሌዎች ነዉ ሐ.በዳኞችነዉ መ. ለናሐ መልስናቸዉ

9.ተከራካሪዎች ክርክራቸዉን የሚጀምሩት?

ሀ.ሰላምታ በመስጠት ለ.ራስን በማስተዋወቅ ሐ.ፊት ለፊት በመቆም መ.ሁሉም

10.የክርክር አዘገጃጀትና አቀራረብ የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ.ዳኝነትን አምኖ መቀበል ለ.ተገቢ ያልሆነ እንቅስቃሴ አለማሳየት

ሐ.ለክርክሩ የተሰጠዉን ጊዜ ማክበር መ.ሁሉም

፬.ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1. ክርክር ለማካሄድ ምን ምን መከናወን አለበት?

2. ክርክር ለምን ያስፈልጋል?

3. ክርክር ማለት ምን ማለት ነዉ፡፡?

የሚከተሉት ቃላት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚሰጡትን ትርጉም ጻፉ፡፡

1.ዋና 4. ሳለ

2.አለት 5.መቶ

3.ገና

**የሚከተሉትን ቃላት ተክክለኛ አዉዳቸዉን በመፈለግአሰገቢ/አስገባና አንቀጽን አሟሉ፡፡**

*መሰሪ ማጥ ሲርድ ባዝራ*

*አግቦ ደባ ፋይዳ አልባሌ*

*ሰዉዩዉ -------------ይመሰል እነጂ፤እንዲህ የዋዛ አይደለም፡፡*

*ሀብትን በተመለከተ----------ከድንጉላ አለዉ፡፡ ታድያ ምን ያደርጋል፤በጎ የማያስን ---------------- ነዉ፡፡ በሰዉላይ ---------ይፈጽማል----------መናገር ያዘወትራል፡፡ይህም መልሶ እራሱን*

*----------ዉስጥ ስለከተተዉ መዉጫ አጥቶ --------ለሌለዉ ነገር እነኳን ትኩረት ሰጥቶ*

*ሲጨነቅ እና ሰዉነቱ---------ይታያል፡፡*

*የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች፡፡*

1.ልቦለድ ማለት ምን ማለት ነዉ

2.የረዥምና ቸችር ልቦለድ ልዩነት ምንድነዉ

3.ልቦለድ አንብባችሁ ታዉቃላችሁ ያነበባችሁትን በአችሩ ግለጹ

**ልብ ወለድ**

***ወንድማማቾች***

**ጊዜዉ ከሁለተኛ የአለም ጦርነ ከሀያ አበኂላ ነዉ ፡፡ ቦታዉ"ጃኑዳ" የሚባል ዉብ ከተማ ሲሆን የከተማዉ የትምህርት ቤት ስም ዘነበ ሲሆን፣ በልዩ የሚባል ወንድም ነበረዉ፡፡ ወንድማማቾቹ ለወላጆቻቸዉ እንደ አህ ያ ጡት ሁለት ሲሆኑ ፣ በልጅነት እድሜያቸዉ እርስ በራሳቸዉ በታም የሚተሳሰቡ ና የሚሰሩትን ስራ ሁሉ በአንድነት የሚያከናዉኑ ነበሩ፡፡ወታደር ለመሆን በአንድነት ተመዘገቡ፣ ወደ ጦርነት በአንድነት ዘመቱ ፤በአንድ የጦር ክፍል ዉስጥ በአንድነት አገልግለዉ በአንድ ጊዜ የአስር አለቃነት ማዕረግ አገኙ፡፡ ከጦርነት ሲመለሱም የከተማዉ ነዋሪ "ቁም ነገረኛ ወጣቶች" እያለ ያሞካሻቸዉ ነበር፡፡**

ከዚህ በኂላ አባታቸዉ ሞቱ፡፡ የአባታቸዉ ንብረት እኩል ለሁለት ለመካፈል የማይመች ነበር፡፡ ስለዚህ እቃዉ ለጫራታ ቀርቦ እያንዳንዱ የፈለገዉን ከገዛ በኂላ፤ ገዘቡን ለሁለት ለመካፈል ተስማሙ፡፡ በዚህመልክ ንብረቱ ተሸጦ ተካፈሉ፡፡ ነገር ግን፣ አባትየዉ ባካባቢዉ አንድም ሰዉ ያላደረገዉ አይነት ትልቅ ወርቅ ሰዓት ነበራቸዉ፡፡ሰዓቱ ለጫራታ በቀረበ ጊዜ ሁለቱ ወንድማማቾች መቻረት ሲጀምሩ፡ሌላዉ ተጫራጭ ህዝብ ለቆላቸዉ ከጫራታዉ ወጣ፡ በዚሁ ጊዜ ዘነበ ያሰበዉ፡ በልዩ ይለቅልኝና እኔ እወሰዳለዉ የሚል ነበር፡፡ በልም በበኩሉ እንዲህ ይመኝ ነበረ፡፡ጫራታዉ ቀጥሎ አንድ ሺ አምስት መቶ ብር ደረሰ፡፡በዚህን ጊዜ ዘነበ፣ “ወንድሜ “የሚሰራዉ ስራ ጥሩ አይደለም” ብሎ አሰበ፡ ስለዚህም አንድ ሺ ስድስት መቶ ብር እሰኪደርስ ድረስ እሱም በበኩሉ ዋጋዉን ከፍ አደረገ፡፡ በልዩ አሁንም ከቻራታዉ እነዳልወጣ ባየ ጊዜ፣ በእዉነቱ ጥሩ ስራ አይሰራም፣ እንዴት እኔ የዋልኩለትን ዉለታ ሁሉ ችላ ብሎ ጫራታዉን ያንርብኛል ፤ወድያዉም እኮ ታላቅ ወንድሙ ነበርኩ”ብሎ አሰበ፡፡ከዝ በኂላ ስዓቱ ወጋ አንድ ሺ ስምንት መቶ ብር በላይ ወጣ ፡፡ በልዩ ከፍ አድርጎ መስጠቱን አላቋረጠም፡፡ ከዝየም ዘነበ በአንድ ጊዜ ሁለት ሺብር አደረሰዉና ወደወንድሙን ዞር ብሎ እንኳን አልተመለከተም፡፡ በጫራታዉ አደራሹ ፀጥታ ሰፈነ፡፡ አጫራቹ ብቻ የተጠራዉን ዋጋ እየመላለ ይናገር ነበር ፡እዚያ ቦታ ብዙ ሰዎች ቆመዉ ይመለከቱ ስለነበር፡ በልዩም፣ “ወንድሜ በነዚህ ሰዎች መካከል መሳቅያ ሊየደርገኝ አይችልም” በማለት፣ ሁሉንም ጫራታዉን በመቶ ብር ከፍ አደረገ፡፡ ዘበነ ድንገት በሳቅ ፈንድቆ፡ “ሶስት ሺ ብር እና የኔን ወንድምነት በዚሁገር”ካለ በኂላ፣እየሮጠ ከአደራሹ ወጥቶ ሄደ፡፡ ዘበነ ፈረሱን ለ እየጫነ ለመሄድ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ እንድስዉ ካደራሹ ወጥቶ ወደርሱ ቀረበና ‹‹ሰዓቱ ያንተ ነዉ፤ በልዩ ተሸንፏል›› አለዉ፡፡ይሄንን እንዳወቀ፣ ወዳዉኑ ጠፀፀት ስሜት ተሰማዉ፡፡ በዚህን ወቅት ስለ ወንድሙ እንጅ ስለ ሰዓቱ አላሰበም ነበር፡፡ “ ወደቤቱ ልሂድ? ወይስ ልቅር? እየለ ግራ ተጋብቶ ቆመ፡፡ የጫራታዉ ታዳሚዎች ካዳራሹ ወጡ፤ በልዩም ከመካከላቸዉ ነበር፡፡ ወንድሙ ለመሄድ ተዘጋጅቶ ባየ ጊዜ፣ ሀሳቡን እንደ ለወጠ ተረዳና፣ “ስለ ሰዓቱ አመሰግናለሁ ዘበነ፣ ከእንግዲህ በኂላ ወንድምህ አንተን እተከተለ የሚሄድበትን ጊዜ ደግመህ አታየዉም!”በማለት፣ ጮክ ብሎ ተናገረ፡፡‹“አንተም! እኔ ላንተ እሰራ የነበረዉ ሁሉ ፈፀሞ ደግመህ አታየዉም!” ብሎ ሲመልስለት፣ ነብርሆኖ ነበር፡፡ ወድያዉ ፈረሱ ላይ እምር በሎ ወጥቶ እየ ጋለበ ሄደ፡፡ ከዚያን ጊዜ በሆኂላ ከአባታቸዉ ገር አብረዉ ይኖሩበት የነበረዉን ቤት እግራቸዉ ረግጦት አያዉቅም፡፡

በልዩ  ከጥቂት ጊዜ በላ የአንድ ድሃ ገበሬ ልጅ አገባ፡፡ ነገር ግን ወንድሙን ለሰርግ አልጋበዘዉም፡፡ ባገባ በአንድ አመቱ፣ ከቤቱ ራቅ ብላ ታስራ ሳር ትበላ ነበረች አንድ ላሙ ሙታ ተገኘች፡፡ የአሟሟቷን  እነቆቅልሽ ማንም ሊፈታዉ አልቻለም፡፡ተመሳሳይ መጥፎ እድሎች  ተከታተለዉ  ደረሱበት፡፡ይባስ ብሎም፣ በክረምት ወቅት የድርቆሽዳሱ ከበርካታ ንብረቶች ጋር ተቃጠለ፡፡ እሳቱ ኬት እንደ ተነሳ ግን  አልነበረም፡፡ “ይህ  ሁሉ የተደረገዉ እኔን  ለመጉዳት ያሰበ ሰዉ ነዉ፡፡” በማለት ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ ሰማዩ በላዩ ተደፋበት፡፡ ደሃ እየሆነ ስለሄደም የመስራት ፍላጎቱ ተዳከመ፡፡ ቤቱ ዉስጥ ቁጭ ብሎ ሲተክዝ መዋል አበዛ፡፡ ከእሳት ቃተሎ በኋላ አንድ ቀን ምሽት ላይ፣ ዘበነ ወደ ወንድሙ ቤት ሄደ፡፡ በልዩ አልጋዉ ላይ ጋደም ብሎ ነበር፡፡“ምን  ልትፈልግ ነዉ እዚህ የመጣኸዉ?” ብሎ ፣ከመኝታዉ ብድግ በማለት  ወንድሙ ላ አፈጠጠ፡፡“ልረዳህነዉ የምፈልገዉ በ ልዩ! በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ላይ ነህ”በማለት መለሰለት፡፡  ”አዎ! የኔ ደግ ሰዉ¡ ልተረዳኝ መጣህ”¡ አለና “አንተ ከምትመኝልኝ፤ የበለጠ  አልደረሰብኝም፤ ከፊቴ ወግድልኝ፤ ካለዚያ ምን እንደሚሆን እግዜር ነዉ የሚያዉቀዉ!”  ሲል  አይኑን አጉረጠረጠበት፡፡ ዘበነ ወንድሙ ደሙ መፍላቱን  ባጊዜ፣ ወደ ኋላ አንድ እርምጃ ፈቀቅ በማለት ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ፣“ሰዓቱን ከፈለከ መዉሰድ ትችላለህ” አለዉ፡፡ በልዩ ግን አሁንም“ወግድልኝ!” ሲል አምቧረቀበት፡፡ ዘበነም ከዚህ በኋላ  መቆየቱ ዋጋ የሌለዉ መሆኑን  ስላወቀ፣ወንድሙን ትቶት ሄደ፡፡

ከዚህ ቀን በፊትም ቢሆን ዘበነ በየጊዜዉ  ስለወንድሙ  ያሰብ ነበር፡፡በተለይ አደጋ ከደረሰበት በኋላ  አስተሳሰቡ  ተለዉጦ ነበር፡፡  ቤተክርስቲያን ሄዶ  ግንኙነታቸዉን ለማሻሻል ቃል ገብቷል፡፡ ነገር ግን ይሄንን ለመፈፀም  ልብ አላገኘም፡፡ አንድ እሁድ ቀን  ቤተ ክርስትያን በሄደ ጊዜ፣ወንድሙ በልም እዝያዉ ነበር፡፡ ገርጥቶና ከስቶ፣ያረጀና የተጣጠፈ ልብስ ለብሶ ተመለከተዉ፡፡

በዚህን ጊዜ ወንድሙ ለርሱ እንዴት ያለ ሩሩና ጨዋ ልጅ  እንደነበረ ማስታወስ ጀመረ ፡፡ “የመጣዉ ቢመጣ ዛሬ ከወንድሜ ጋር እታረቃለሁ” ብሎ ለፈጣሪዉ ቃል ገባ፡፡ ከወንድሙ ጎን ለመቆም ቆረጠ፡፡ ይሁን እንጂ፣ በመካከላቸዉ ሚከልል ነገር መኖሩን ዘነበ ልብ አላለም፡፡ ከቅዳሴዉም በኋላ  ሚስቱ ልትሆን ትችላለች ብሎ የጠረጠራት ሴት አጠገቡ እንዳለች አስተዉሏል ፡፡ በርካታ ሰዎች በአካባቢዉ  ስለነበሩ “እቤቱ ሄጄ ረጋብይ ባናግረዉ ይሻሻላል” ብሎ ወሰነና  ወደ ቤቱ ተመለሰ፡፡

### የንባብ ጊዜ ጥያቄ

1.ታሪኩ ምን ሊሆን እንደሚችል ገምታችዋል?

2.ቀጣዩ ሀሳብ ምን ሊሆን ይችላል?

3.እስካሁን ካነበባችሁትምንምን ታስታዉሳላችሁ?

ቀኑ ስመሽ ወደ ወንድሙ ቤት አመራ፡፡ በሩ አጠገብ ሲደርስም ትንሽቆምብሎ እደ ማሰብ ሲል፣ ከቤት ዉስጥ የራሱ ስም ሲጠራ ሰማ፡፡ " ወንድሙ ሚስት ነበረች፡ ስሙን እያነሳች የምትናገረዉ ወንድምህ ዛሬ ቆረበ እኮ! እርግጠኛ ነኝ ስላንተ ያስብ ነበር" አለች፡፡

"እባክሽ ስለኔ አይደለም፤ ስለራሱነዉ የሚያስበዉ" "አለ፣በልዩ፡፡ ከዚያ በኋላ ለረጅም ጊዜ ድምፅ አልተሰማም፡፡ ጥቂት ቆየና ዘነበ እዚያዉ እንደቆመ፡ ላብ አጠመቀዉ፡፡ የምድጃዉ እሳት እየተንጣጣ የነበልባሉ ድምፅ የሰማል፡፡ በልዩ ወደዉጭ ለመዉጣት ከተቀመጠበት ተነሳ፡፡ ዘነበ ቶሎ ብሎ ዛፍ ስር መደበቅ ነበረበት፣ ተደበቀ፡፡ በልዩ አንድ እቅፍ እንቸት ለማስገባት ፡ ወንድሙ ወደ ተደበቀበት ዛፍ አመራ፡፡ የዘነበ የልብ ምት ጨመረ፡፡አሁንም እየተጠጋዉ መጣ፡፡ዘነበ ትኩር ብሎ አየዉ፡፡ በልዩ የጥንት የደንብ ልብሱን (የወታደር)ልብሱን ለብሷል፡፡ "እነዚህን ልብሶች ሁለተኛ አንለብሳቸዉም ለልጆቻችን እናወርሳቸዋለን" ተባብለዉ ቃል ገብተዉ፣ እንደ ነበረ አስታወሰ፡፡ ከልቡ ምት መጨመር ጋር፣ በኪሱ የያዘዉ ወርቅ ሰዓት ቲክቲከታማ ይሰማ ነበር፡፡ በልዩ ፣እህህ!" ተነፈሰና፡ ተዘዋዉሮ ሳይመለከት እቅፍ ሙሉ ጭራሮዉን ይዞ ሲመለስ፡ ወንድሙን በጣም ተጠግቶ ያልፍ ስለነበረ፣በጭራሮዉ ጫፍ ፊቱን ቧጭሮት አለፈ፡፡ ከአስር ደቂቃ ቆይታ በኋላ ከዛፍ ስር በመዉጣት፡ የወንድሙን ወደቤቱ መግባት እዳረጋገጠ ሌላ ዘዴ መፈለግ ያዘ፡፡ ከአመድ ማጠራቀሚያዉ በርሚል ከሰል በመዉሰድና ጭራሮ ለቃቅሞ ወደ ድርቆሽ ደስ በመግባት እሳት አነደደ፡፡ በእሳቱ ብርሃንም ወንድሙ ፋኖስ የሚሰቀልበትን ሜንጦ ስላየ ሰዓቱን በሜንጦዉ ላይ አንጠልጥሎ ፍሙን በማጥፋት ወደ ቤቱ አመራ፡፡ ጭንቀቱ ስለ ተቃለለለትም፣ በዚያ ቅዝቃዜ ሲሮጥ የወጣትነት ሀይል የይሰማዉ ነበር፡፡ በሚቀጥለዉ ቀን የድርቆሹ ዳስ ተቃጥሎ ማደሩን ሰማ፡ ምናልባት፡ ማታ የነደደዉ እሳት ፊጹም ሳይጠፋ ሳያቃጥለዉ አልቀረም ይሆናል፡፡ ይህም ሁኔታ ዘነበን በጣም አሰዘነዉ፣ ሀፍረትም ለበሰ፡፡ ከዚያ የፀሎት መዝሙሩን አዉጥቶ ጮሀ

ብሎ ዘመረ። ይሄንን የሰሙ ያካባቢ ሰዎች፡ የሆነ ነገር እንደ ደረሰበት ጠረጠሩ። ቀኑ በጨለማ ሲተካ ዘነበ በጠፋ ጨረቃ ወደ ወንድሙ ቤት በመሄድ ከቃተሎዉ መካከል አንድ ቦታ ቆፍሮ አንድ ነገር አወጣ፡ ከዚያ ሰዓት ቀረዉ አንድ የተጨባበጠ ወርቅ ነበር። ይሄንን በመይዝና ወደ ወንድሙ ዘንድ በመሄድ፣ ሁሉን ነገር ለመግለፅና እንደገና ለመታረቅ ፈለገ። ነገር ግን "እንዴት አድርገህ ዛሬ ደፍረህ ትሄዳለህ ?" ብለዉ፡ አስጠነቀቁት። ምክንያቱም ፣ አንዲት ተንሽ ልጅ ቃጠሎዉ መካከል ቆሞ ሲቆፍር ማየጠቷን ተናግራለች። የአካባቢዉ ነዋሪ ወጣቶችም፡ ደሱ የተቃጠለ እለት ዘነበን ወደ ወንድሙ ቤት ሲሄድ እንዳዩት ተናግረዋል። በማግስቱ ሰኖም፣ የጠባይ ለዉጥ ማሳየቱን ሁሉም ሰዎች ያዉቁ ነበር። የአካባቢ ባለ ስልጣኖችም ይህ መረጃ ስለ ደረሳቸዉ ለማጣራት ወስነዋል በልዩደግሞ እነእህ ሁሉ ወሬዎች ደርሰዎት ስለ ነበረ፣ ድርጊቱን የፈፀመዉ ወንድሙ እንደሆነ አምኖ ተቀብሏል።በዚህ ሁኔታ እያለ ነበር ፡ ጉዳዩን ለማጣራት ለሁለቱም ጥሪ የደረሳቸዉ።ዘነበ ጥሩ ልብሱን ፣ በልዩ ደግሞ ጭርንቁሱን ለብሰዉ ሁለቱም ምርመራዉ ቦታ ተገኙ።ዘነበ ወንድሙን ተመለከተዉ። በልዩም አስተዋለዉ።በልዩ፡ ወንድሙ ይቅርታ እየጠየቀዉ መሆኑን ዓይኑ እንደሚናገር አመነ።"ስለእርሱ ምንም ነገር እንዲናገር አልፈለገም ማለት ነዉ " ብሎ አሰበ። በልዩ። ስለዚህም በድርጊቱ ወንድሙን የሚጠረጥረዉ እንደሆነ ሲጠየቅ፣ድምፁን ከፍ አድረጎ በመጮህ "አልጠረጥረዉም" አለ፡ከዚያን ቀን በኋላ ፣በልዩ አልኮል በብዛት መጠጣት ጀመረ፣ ሁኔታዎች ሁሉ ተበላሹ፣ዘነበም ቢሆን፡ ምንም እንኳን መጠጥ ባይጠጣ፡ መልኩ ስለተለዋወጠና ስለተጎሳቆለ፣ ስሱ መሆኑን ለማወቅ አዳጋች ሆኖ ነበር። አንድ ቀን ማታ ዘበነ ወደ ተከራያት ትንሽ ክፍል አንድት ድሃ ሴትዮ ገብታ ከሷ ጋር እንድሄድ ጠየቀችዉ፡ ፡ የወንድሙ ባለቤት ነበረች ። ምንም ሳይናገር ተከትሏት ሄደ። በሩ መግቢያ ላይ ሲደርሱ፣ ሚያንገሸግሽ ሽታ ሸተታቸዉ። በል አልጋ ላይ ሆኖ ፣ያለ የሌለዉ የልብስ ዓይነት ተጭኖበት፡ ገርጥቶ ከስቶ፡ ዓይኖቹ ጎድጉደዉና ከሰዉነት ጎዳና ወጥቶ ሲመለከተዉ የዘነበ ጉልበት ንፋስ እንደነካዉ ቄጤማ አረገደ። ከአልጋዉ ታች ተቀምጦም እርር ብሎ አቀሰ። ከዚያ በኋላ ሁለቱ ወንድማማቾች መነጋገር ጀመሩ። ከጫራታዉ በኋላ ፣ አሁን እስከ ተገናኙበት ጊዜ ድረስ የሆነዉን ነገር ሁሉ ገላልጠዉ አወሩ። ዘበነ የቀለጠዉን የወርቅ ሰዓት አወጣና ለወንድሙ አሳየዉ። ይህንን ያህል ጊዜ ተለያይተዉ ሲኖሩ አንዳጭም እንኳን የተደሰቱበት ጊዜ እንዳልነበረ ተገላለጡ። በልዩ አቅሙ ደክሞና ታሞ ስለነበረ፡ ዘ ነበ ከአልጋዉ አጠገብ ሳይለይ አስታመመዉ። አንድ ቀን ጢዋት በልዩ ከእንቅልፉ ሲነቃ፣ "ዛሬ ፍጹም ድኛለሁ " "ከእንግዲህ ወንድሜ ሁልጊዜ ሳንለያይ እንደ

ቀድሚአችን  አብረን እን ኖራለን" አለዉ ። ሆኖም በዚያ ቀን አረፈ።ዘነበ  የወንድሙን ባለቤትና ልጁን ወደበቱ ይዞ በመሄድ፡ ተንከባክቦ አኖራቸዉ።እሱም በአካባቢ ሰዉ ተከበረ ምራቁን የዋጠ ሰዉ ሆነ ። ሽማግሌዉ የአስር አለቃ  የተምህርትቤት ዳይሬክተር የሆነዉን፣ ለአካባቢዉ ህዚብ    አንድ ዉለታ ጥሎ ለማለፍ  ስለፈለገ ነበር። በህጻናቱ ጠባይ ላይ እንዲቀረጽ የሚፈልገዉ ነገር ቢኖር፡ መጀመርያዉም መጨረሻዉም ፍቅር ነበር። እናም፣ ሰዉ ማፍቀር  ለታዳጊዎች አስተማረ። ህጻናትእየመጡ እንደጓደኖቻቸዉ ና እንደ አባታቸዉ ያጫውቱት፣ ችግራቸዉንም ያወያዩት ነበረ፡

የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች   የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የተዘጋጀ ይህ ፈተና ሲሆን (7)ሰባት ክፍሎችን  በዉስጡ አካቶ የያዘ ነዉ።

አንደኛዉ በምንባቡ መሰረት እዉነት ወይም ሀሰት በማለት የሚሞላ 10ጥያቄ ሲሆን ሁለተኛዉ ለፈሊቶች ተመሳሳይ ፍቺ መስጠት 10 ጥያቄ (3)ሶስተኛዉ በምንባቡ መሰርት ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ በመምረጥ መልስ (4) አራተናዉ ቃለት ሲጠብቁና ሲላሉ የሚሰጡትን ፈቺ ማሳየት የሚል 5 ጠያቄ (5) አምስተኛዉከቃላት ነጻናጥገኛ ምእላድ መሌት የሚል 5 ጥያቄ (6) ስድስተኛዉ ባዶ ቦታዉን በምንባቡ መሰረት  መሙላት የሚል 5 ጥያቄ (7) ሰባተኛዉና የመጨረሻዉ በምንባቡ መሰረት ለጥያቄዉ አጭር መልስ ስጥ የሚል(6) ጥያቄዎችን የያዘነዉ ጥያቄዎችን በአጠያየቅ ስልታቸዉ መልሷቸዉ።

**የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች   የአንብቦ መረዳት ችሎታ ለመለካት የተዘጋጀ  ፈተና**

፩.የሚከተሉትን ጥቂዎች በምንባቡ መሰረ ትትክክል ከሆነ እዉነት ትክክል ካልሆነ ሀሰት በማለት መልሱ።

1.ወንድማማቾች ለቤተሰቦቻቸዉ ሁለት ብቻ ናቸዉ።

2. የበልዩ ባለቤት ወንድማማቾች እንዲታረቁ ስትፈልጋለች

3.በጫራታዉ የቀረበዉ እቃ የወርቅ ሰዓት ነበረ።

4. በጫራታዉ ላይ ብዙ ሰዎች ተሳትፈዋል።

5.የዉርስ ንብረት በጫራታ የቀረበበት ምክንያት የሁለቱ ወንድማማቾች አለመስማማት ነዉ።

6.የቀለጠዉን የወርቅ ሰዓት አዉጥቶ ለወንድሙ ያሳየዉ ዘበነ ነዉ።

7.ዘበነ የትምህርትቤቱ ዳሬክቴር ነዉ፡፡

8.ሁለቱ ወንድማማቾች ወደ ጦርነት በአንድ ጊዜ ዘምተዋል፡፡

9.የሁለቱ ወንድማማቾች አባት የሞተዉ እነሱ እንደ ተወለዱ ሰነዉ፡፡

10.የድሃዉን ገበሬ ልጅ ያገባዉ ዘበነ ነዉ፡፡

፪.ቀጥሎ በ‹‹ሀ›› ረድፍ ስስር ለቀረቡት ቃላትና ፈሊጥ በምንባቡ መሰረት ተመሳሳይ ፍቻቸዉን በ‹‹ለ›› ረድፍ ከተዘረዘሩት በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| ‹‹ሀ›› | ‹‹ለ›› |
|---|---|
| 1.ሰማዩ በላዩ ላይ ተደፋበት | ሀ.ሞተ |
| 2.ደሙፈላ | ለ.ተናደደሰ |
| 3.ጭርንቁስ | ሐ.አዘነ |
| 4.ፀጋ | መ.ቆሻሻዉ/አሮጌዉ |
| 5.ያሞካሻሉ | ሠ.ያመሰግናሉ |
| 6.ታዳሚዎች | ረ.ተሳታፊ |
| 7.ያንርብኛል | ሰ.የሰወድድብኛል |
| 8.አምባረቀበት | ሸ.ጮሀበት |
| 9.አረፈ | ቀ.አዋቂ ሰዉ |
| 10.ምራቁንየዋጠ | በ.ስጦታ |

፫.የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክለኛዉን መልስ የያዘዉን ሆሄ በመምረጥ መልሱ፡፡

1.እነዚህ ወንድማማቾች------- የሚባል ከተማ ዉስጥ ነበረ፡፡

ሀ. አዲስአበባለ ለ.ጃኑዳ ሐ.ዝዋይ መ.ጎጃም

2.ወንድማማቾች በአንድ የጦር ክፍል ዉስጥ የ------ማዕረግ አገኙ።

ሀ.አሰርአለቃ ለ.አምሳለቃ ሐ.መቶአለቃ መ.ሻለቃ

3.ሞቱ የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍል ---------ነዉ።

ሀ.ተወሳከግስ ለ.ቅፅል ሐ.ግስ መ.ስም

4. ወታደር ይህ ቃል፡-

ሀ.የጥቅልስም ለ.የማዕረግስም ሐ. የሙያስም መ.ሀናሐ

5.እምርብሎ የተሰመረበት ቃል ፍቺ።

ሀ.ተናዶ ለ.እየሮጠ ሐ.ዘግይቶ መ.መልስየለዉም

6.አይኑን አጉረጠረጠበት የተሰመረበት የቃል ፍቺ።

ሀ.ጨፈነበት ለ.አፈጠጠበት ሐ.አርገበገበበት መ. መልስየለዉም

7. ከወንድሙ ጎን ለመቆም ቆርጦ ተነሳ የተሰመረበትቃልፍቺ

ሀ.ተነሳ ለ.ወሰነ ሐ.አሰበ መ. ሀናሐ

8. በልዩ ያገባት ልጅ የ----ልጅናት

ሀ.የአስተማሪ ለ.የገበሬ ሐ.የሹፌር መ.የዶክተር

9.ከሁለቱ ወንድማማቾች ዉስጥ ከሰዉነት ጎዳና የወጣዉ ማነዉ?ሰ

ሀ.ዘበነ ለ.በልዩ

10.ልብ አላገኘም የተሰመረበት የፈሊጥ ፍቺ?

ሀ.የዉስጥ የሰዉነት አካል ለ.የመወሰን አቅም አልነበረዉም

ሐ.አልበላም መ.ፈራ

፬.የሚከተሉትን ቃላት ሲጠብቁ ና ሲላሉ የሚሰጡትን ፍቺ በአረፍተነገር ዉስጥ በማስገባት አሳዩ።

1.ገና 2.ዋና 3.ሳለ 4.አላት 5.ይመራል

ጥገኛ ምዕላድ የሚከተሉትን ቃላት ነፃ ና ጥገኛ ምዕላድ በመለየት አሳዩ

| ተ/ቁ | ቃል | ነጻ. ምዕላድ | ጥገኛ ምዕላድ |
|---|---|---|---|
| 1. | ሰዎች | | |
| 2. | ላሚት | | |
| 3. | እስራሶች | | |
| 4. | ቤቶች | | |
| 5. | መምህራኑን | | |

ባዶ ቦታዉን በምንባቡ መሰረት አሟሉ፡፡

1.ዘበነ ና በልዩ --------------ነበሩ፡፡

2.ለጫራታ የቀረበዉ ሰዓት -------- የሰዓት ነበር ፡፡

3.ከሁለቱ ወንድም አማቾች መካከልሚስት ያገባዉ----------ነዉ፡፡

4.ጊዜዉ ከሁለተኛዉ የአለምጦርነት ---------ዓመት በኋላ ነዉ፡፡

5.በሳቅ የፈነደ ቀዉ ----------ነዉ፡፡

፫.በምንባቡ መሰረት ለጥያቄዎች አጭር መልስ ስጡ፡፡

1.ታሪኩ ስለ እነማን ያወራል?

2.የታሪኩ መቼት ምንድ ነዉ?

3.የታሪኩ ሀሳብ ምንድነዉ?

4.ታሪኩ አጭር ወይስ ረዥም ልቦለድ?

5.ከታሪኩ ምን ምን ተማራችሁ?

አባሪ 5

በጅማ ዩኒቨርሲቲ

የሶሻል ሳይንስ እና ሂዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ- ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መረሃ ግብር

በተማሪዎች የሚሞላ የፅኑፍ መጠይቅ

ይህ የፅሁፍ መጠይቅ የተዘጋጀዉ ተማሪ ተኮር የመማር ማስተማር ዘዴ ለተማሪዉ አንብቦ መረዳት ያለዉ አስተዋጽኦ በሚል ርእስ ለሚሰራዉ ምርምር መረጃ ለመሰብሰብ ነዉ፡፡

ጥያቄዎችን በትክክል በመገንዘብ ከቀረቡት ቸማራጮች መካከል አንድ መልስ ብቻ እንድትጨ/እንድትሰጥ፡፡

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አራት አማራጮች ቀርበዋል በመረጣችሁት ምረጫ ስር (x) ምልክት አድርጉ፡፡

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፈተኛ | በጣም ከፍተኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ከልምምድ በፊት መምህራቸሁ በምንባቡ ዙርያ የቀደመ እዉቀት እንዳለሽ/እንዳለህ በመለየት ፍንጭ ይሰጣሉ? | | | | |
| 2 | ከልምምድ በፊት ለምን እና እነዴት እንደምታነቡ ሀሳብ በመስጠት? ያበረታቱሻል/ያበረታቱሀል? | | | | |
| 3 | ምንባብ ለማንበብ ፍላጎት አለህ/አለሽ? | | | | |
| 4 | መምህሯ የትምህርት መርጃ መሳርያ ትጠቀማለች? | | | | |
| 5 | መምህሯ የቤትስራ ትሰጣለች? | | | | |
| 6 | ለንባብ ተነሳሽነት እንዲኖራችሁ ታደርጋለች? | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 7 | መምህሯ ከምንባቡ ለወጡ መልመጃዎች በዉይይት በመሳተፍ እንድተሰሩ ታደርጋለች? | | | | |
| 8 | ገዚህ በፊት ስላነበባችሁት ምንባብ ስላጋጠማችሁ ገጠመኝ ሀሳብ እንድት ሰጡ ታበረታታለች? | | | | |
| 9 | ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለምትጠየቂዉ /ለምትጠየቀዉ ጥያቄ መልስ ትሰጫለሽ/ትሰጣለህ? | | | | |
| 10 | ሀሳብሽን/ሀሳብህን በነፃነት ትገልፃለሽ/ጽገልፃለህ? | | | | |
| 11 | መምህሪቷ ለማስተማር ወደ ክፍል ስትገባ ተዘጋጅታ ትገባለች? | | | | |
| 12 | መምህሪቷ የተማሪዎችን ፍላጎት ለማወቅ ንቁ ናት? | | | | |
| 13 | የመምህሪቷ ንግግር እና ተግባር ይጣጣማል? | | | | |
| 14 | የምትሰራዉ /የምትስሪዉ ስራ ስህተት ካለዉ መምህረዋ ማስተካከያ ትሰጣለች? | | | | |
| 15 | ይህ የንባብ ትምህርት የማንበብ ችሎታሽን /ችሎታህን አሳድጓል? | | | | |